፫ ፡ የሱስ ፡ የሚመራኝ፡መንገድ ፡
ሰላምና ፡ ደስታ ፡ ነው ።
ተስፋዬም ፡ ፍጹም ፡ ዕረፍት ፡ ነው ፡
በሰማይ ፡ ቤቱ ፡ ካለው ።
ወደ ፡ ሕይወት ፡ ይመራኛል ፡
ሊያደርሰኝ ፡ ወደ ፡ ተስፋው ፡
ስለዚህ ፡ እቸኩላለሁ ፡
ለሚያደርግልኝ ፡ ተስፋው ።
ስለዚህ ፡ እቸኩላለሁ ፡
ለሚያደርግልኝ ፡ ተስፋው ።

ዕርገቱ ።

ፍየ

S. T. 225.

፩ ፡ አያለሁ ፡ የሱስ ፡ ዕርገትህን ፡
ስታርግ ፡ ከምድራችን ።
እኔ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡
ልኖር ፡ በውርደት ፡ ገና ።

ኃዘን ፤ ድካም ፡ ተከተለኝ ፤
ገና ፡ ካባቴ ፡ ቤት ፡ ሩቅ ፡ ነኝ ።
፪ ፡ ያን ፡ ክቡር ፡ አገር ፡ በእምነት ፡
አውንም ፡ ልመልከት ።
ከኃጢአቱ ፡ ተፈትቼ ፡
ልከብር ፡ በጌታዬ ፡
ልኖር ፡ ከብፁዓን ፡ ጋራ ፡
በሕያው ፡ አምላክ ፡ ከተማ ።
፫ ፡ በወዲያ ፡ የለም ፡ ሌሊት ፡
ጨለማ ፡ ኃዘን ፡ ሞንቀት ።
በዚያ ፡ አለ ፡ መዝገቤ ፡
በዚያም ፡ ይሁን ፡ ልቤ ።
ከየሱስ ፡ ይኑረኝ ፡ ኅብረት ፡
ጸጋ ፡ ይስጠኝ ፡ ልኖርለት ።
፬ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፤
ሊመለስ ፡ ወደ ፡ እኛ ።
ለሥራዬ ፡ እንድቀና ፡
በጸሎት ፡ እንድተጋ ፡

እስከ መጣ ፡ ባልታሰበው ፡
ዕለት ፡ ዕለት ፡ ልጠብቀው ።
ፅ ፡ ትጉ ፡ ሎሌ ፡ የሚሠራ ፡
ብዙ ፡ ነው ፡ ስትመጣ ።
ተስፋ ፡ ሰጠህ ፡ እንደሚወርስ ፡
ያን ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥት ።
ልታድለው ፡ ክብረት ፡ ደስታ ፡
በልዑል ፡ አባትህ ፡ ግርማ ።

ሉንዳል ። — O. E.

ጸራቅሊጦስ ።

ሮቻ

S. T. 229.

፩ ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡
የእውነት ፡ መንፈስ ፡
መጥተህ ፡ ምራን ።
አበርታን ።

ኃይል ፡ ሲጐድልብን ፡
እምነት ፡ ጨምርልን ፡
በየዕለት ፡ ወደ ፡ ብዕዕና ፡ ሳበን ።
ጥበብ ፡ አቤቱ ፡ ስጠን ፡ ከአርያም ።
፪ ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡
የሥልጣን ፡ መንፈስ ፡
ነፍስን ፡ አሙቅልን ።
በየልባችን ፡
ፍቅርን ፡ አስርጽብን ።
እንደ ፡ ፍሬ ፡ ሊወጣ ፡
የውሀት፡ትዕግሥት ሰማያዊ፡ደስታ።
ጽድቅን ፡ አቤቱ ፡ ስጠን ፡ ከአርያም ።
፫ ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡
የደስታ ፡ መንፈስ ፡
ደስታን ፡ አውርድልን ።
በመከራችን ፡
አትግለልብን ።
በመሸብን ፡ ዕለት ፡

ብርሃን ፡ ሁነን ፡ ሰላም ፡ በልብ ፡
አግባበት ።
አምላክ ፡ ብዕዕናን ፡ ስጠን ፡ ከአርያም ።

O. E.

ፎፀ

S. T. 232

፩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡
በልቤም ፡ ውስጥ ፡ ብርሃን ፡ አብራ ።
በአንተ ፡ እንድጸና ።
እውነትህን ፡ አስተምረኝ ፡
በቀና ፡ መንገድም ፡ ምራኝ ፡
ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነኝና ።
፪ ፡ በእውነት ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡ ምራኝ ፡
ወዳንተም ፡ እንድቀርብ ፡ ጥራኝ ፡
በቃልህም ፡ እዘዘኝ ።
ከክፉውም ፡ ተለይቼ ፡
ከኃጢአትም ፡ ጠርቼ ፡
ልከተልህ ፡ እገዘኝ ።

፫ ፡ አቤቱ ፡ ጸጋህን ፡ ስጠኝ ፡
ለሁሉ ፡ ዘመንም ፡ እርዳኝ ፡
በሃይማኖት ፡ ልጸና ።
በጌታ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ልኖር ፡ ልድን ፡ ልታገሥም ፡
ረዴት ፡ በአንተ ፡ አለኝ ።
፬ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳያስወድቀኝ ፡
ዓለምም ፡ እንዳይደልለኝ ፡
ከቶ ፡ አትራቅብኝ ።
ለመንፈሴ ፡ መስክርልኝ ፡
ልጅነት ፡ እንደሆነልኝ ፡
ለነፍሴ ፡ ረድኤት ፡ ስጠኝ ።
፭ ፡ ስንፍናዬ ፡ ይሰማኛል ፡
መለመንም ፡ ይሳነኛል ፡
አንተ ፡ ግን ፡ ጸልይልኝ ።
አ ፡ ርኅሩኅ ፡ መንፈስ ፡ በኔ ፡ ኑር ፡
የደከመውንም ፡ ልቤን ፡ ጠብ ፡
ከአብም ፡ ለምንልኝ ።

ጌ ፡ በሰውቀትህ ፡ በጸጋህም ፡
ፍራ ፡ ለማፍራት ፡ ለማደግም ፡
ዘወትር ፡ አነግሣኝ ።
በሰጠኸኝ ፡ ቅዱስ ፡ መክሊት ፡
ዘላለም ፡ የማያልቅ ፡ ጥሪት ፡
እንዳገኝ ፡ አበረታታኝ ።

ጔ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ ሆይ ፡
እርዳኝ ፡
በጭንቀቴም ፡ ሁሉ ፡ አጽናኝ ።
በሞትም ፡ ድምጽ ፡ ስጠራ ፡
እንደ ፡ ምዕመን ፡ እንድሞት ፡
አጠንክረኝ ፡ በሃይማኖት ።
ነፍሴን ፡ ላንተ ፡ አደራ ።

ሱንዳል ፡ ረስቱን ።

ፇፇ

S. T. 21.19. Am. 95.

ፇ ፡ አ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ና፡መጀኔ፡
ልቤንም ፡ ክፈት ፡ ለአንተ ።

ብእውነቱ ፡ የምትመራ ፡
ብእውነት ፡ ልቤንም ፡ ምራ ።
ፎ ፡ የኃጢአት፡ጸጸት፡ ሲሞርደኝ፡
ፍርሃት ፡ ቄንቀት ፡ ሲያውከኝ ፡
በምሕረትህ ፡ ነው ፡ የምታድል ፡
ሰላምም ፡ ነዋሪ ፡ ዕድል ።

ፏ ፡ ከክፉ ፡ ምኞት ፡ ነፍሴን ፡ አንጻ ፡
የጨለመ ፡ ልቤን ፡ አብራ ።
ንገሥ ፡ በርሱ ፡ በቅድስና ፡
ምላበት ፡ ያን ፡ ቅዱስ ፡ ደስታ ።

ፐ ፡ ጠማማ ፡ ፈቃዴንም ፡ አቅና ፡
ቅናትም ፡ በልቤ ፡ አግባ ።
ለአምላክ፡ክብረት፡ለሰውም፡ጥቅም።
እርዳኝ ፡ ለመኖር ፡ በዓለም ።

ሱንዳል ።

ሥላሴ ።

ፑፇ

S. T. 53.1. Am. 131

ፇ ፡ ለአምላካችን ፡ በሰማይ ፡
ይገባዋል ፡ ምስጋና ፡

ስለ ፡ ጸጋው ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡
የሰጠው ፡ ለብዕዕና ።
በምድር ፡ ደስታና ፡ ሰላም ፡
ሲሰጥ ፡ ይገባናል ፡ በጣም ፡
ፈቃዱን ፡ ልንፈጽም ።
፪ ፡ አ ፡ አባት ፡ ስላንተ ፡ ምሕረት ፡
እናመሰግናለን ።
አንተ ፡ በታላቅ ፡ ቸርነት ፡
ጸጋን ፡ አወረድህልን ።
ሥሉጥ ፡ እጅህ ፡ ሁሉን ፡ ይይዛል ፤
ሥዉር ፡ ኃጢአት ፡ ይታይሃል ፤
ዳኝነትህ ፡ ይቀናል ።
፫ ፡ የሱስክርስቶስ ፡ የልዑል ፡ ልጅ ፡
ልታድነን ፡ የመጣህ ፤
ከፍርድና ፡ ከሰይጣን ፡ እጅ ፡
በሞት ፡ እኛን ፡ የዋጀህ ፤
በትልቅ ፡ ምሕረትህ ፡ መጠን ፡
ከመቅሠፍት ፡ ሞት ፡ ልታድነን ፤
በአንተ ፡ ስንማጠን ።

፬ ፡ በመንፈስህ ፡ ልባችንን ፡
በታልህ ፡ አጸናና ።
ላንተ ፡ ምስጋና ፡ መቅደስህን ፡
ብየነፍሳችን ፡ ሥራ ።
በመከራችን ፡ ደግፈን ፡
አድስ ፡ ለጽድቅ ፡ ልባችንን ፡
እምነትን ፡ ጨምርልን ።

ሉንዳል ።

ሮጌ

S. T. 54.

፩ ፡ እናምናለን ፡ በአባት ፡
ባቆመልን ፡ ምድርን ፡ ሰማያት ።
ጥጋችን ፡ ነው ፡
ርኅሩኅ ፡ የዋህ ፡ ለሰው ።
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።
፪ ፡ ሊያድነን ፡ ከሞት ፡ ጥፋት ፡
ክርስቶስ ፡ መጣልን ፡ ከአባት ።

እኛን ፡ ፈጽ ፡
ሆነልን ፡ ቸር ፡ ጌታ ።
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።
ቮ ፡ መንፈሱ ፡ ጸጋን ፡ ያድላል ፡
ይቀድሰናል ፡ በምላክ ፡ ቃል ።
ለነፍስ ፡ ሕይወት ፡
ይሰጣል ፡ በእምነት ።
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።

N.N.

ሮጀ ፡

S. T. 452.25.

ፅ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የሰጠኸን ፡
መድኃኒት ፡ ለሁላችን ፡
በፍቅርህም ፡ የጠራኸን ፡
አ ፡ ርኅሩኅ ፡ አባታችን ፡
ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ቃልህን ፡

ወደኛ ፡ ስደድልን ።
የጨለመ ፡ ልባችንን ፡
በመንፈስህ ፡ አብራልን ፡
በፍቅርህም ፡ ራራልን ።
ፔ ፡ ምሕረትህን ፡ ካልሰጠኸን ፡
ቃሉን ፡ መስማት ፡ አይቻልም ።
እንጮኻለን ፡ አድነን ፡
በመንፈስም ፡ በቃልም ።
እንደ ፡ ጠላትህም ፡ ፈቃድ ፡
ከቅዱስ ፡ ዘርህ ፡ ጋራ ፡
እንዳይደባለቅ ፡ እንክርዳድ ፡
አ ፡ አባት ፡ ለኛ ፡ ራራ ፡
ልባችንንም ፡ አብራ ።
ቮ ፡ ዕዳችንን ፡ በራስህ ፡ ላይ ፡
የጫንክ ፡ መድኃኒታችን ፡
ጕስቍልናችንን ፡ ስታይ ፡
ራራልን ፡ በጭንቃችን ።
አ ፡ የሱስ ፡ ወንድማችን ፡ ነህ ፡

ተስፋህን ፡ ፈጽምልን ።
ጳራቅሊጦስን ፡ ሰጥተህ ፡
እውነቱን ፡ ግለጥልን ፡
ቸር ፡ ጠባቂም ፡ ሁንልን ።

፬ ፡ አ፡ያምላክ ፡ መንፈስ ፡አግዘን ፡
የከይሲን ፡ ወጽመድ ፡ በጥስ ፡
የክርስቶስንም ፡ ኃል ፡ ስጠን ፡
ነፍሳችንንም ፡ ቀድስ ።
በሕይወት ፡ ኃል ፡ ተመግበን ፡
በየሱስ ፡ እንድናምን ፡
ሥላሴንም ፡ እመስግነን ፡
እንድንወርስ ፡ ሰላምን ፡
አንተ ፡ እርዳን ። አሜን ።

ረስቲን ።

ፍ፬

S. T. 538,4. Am. 113.

፩ ፡ ከአምላካችን ፡ማን ፡ይበልጥ ፡
እንደርሱስ ፡ ማን ፡ ይሆናል ፡

ከሃሊ ፡ ኃይሉንም ፡ ሲገልጥ ፡
እንደ፡ት ፡ በጣም ፡ ይገርማል ።
በስድስት ፡ ቀን ፡ በኃይሉ ፡ ኃል ፡
ምድራችንን ፡ አቁምዋል ፡
በርስዋም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ።

፪ ፡ አምላክ ፡ የፈጠረውም ፡ሁሉ ፡
ግሩምና ፡ መልካም ፡ ነበር ።
እባቡ ፡ ግን ፡ በተንኰሉ ፡
እጠፋው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ።
በአባታችን ፡ ኃጢአት ፡
ውርሳችን ፡ ሁንዋል ፡ ጥፋት ፤
በሁሉም ፡ ፍርድ ፡ ተጫነ ።

፫ ፡ ግን ፡አምላክ ፡ሰው ፡ሆኖልናል ፤
በሕይወቱም ፡ በሞቱም ፡
መድኃኒት ፡ ተገኝቶልናል ፡
ከፍርዱ ፡ ከጥፋቱም ።
ፍዳችንን ፡ ተቀበለ ፤
ዕዳችንንም ፡ ከፈለ ፤
ተፈጸመ ፡ ሲል ፡ ሞተም ።

፬ ፡ ይህንም ፡ የሚያምነው ፡
በልቡም ፡ የሚቀበል ፡
ይታጠባል ፡ ከበሽታው ፡
በቅዱስ ፡ ደሙ ፡ ጠበል ።
ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ድንዋል ፡
ለነፍሱም ፡ ሕይወት ፡ ያገኛል ፡
ከወንድሙ ፡ ከየሱስ ።
፭ ፡ በአብ፡በወልድ፡በመንፈስም፡
አገኘን ፡ ደኅንነት ።
ለሥሉስ ፡ አምላካችንም ፡
ምስጋና ፡ ይሁንለት ።
ከሞትና ፡ ከሰይጣን ፡ ኃይል ፡
በየሱስ ፡ ፍጹም ፡ ድነናል ።
መድኃኒት ፡ ሆይ ፡ ተመስገን ።

ረዕቱን ።

፲፫

Am. 52. S. T. 12.

፩ ፡ አባትን ፡ ሰብሐ ፡
ስለ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋው ።

በርኅራኄ ፡
ልጆቹን ፡ ያስባል ።
ወድሱት ፡ እናንት ፡
የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡
የሆዋን ፡ ወድሱት ፡
፪ ፡ ልጁንም ፡ ሰብሐ ፡
ታላቅ ፡ ነው ፡ ቸርነቱ ።
በምሕረቱ ፡
ለሕዝቡ ፡ ያስባል ።
ጎበዞች ፡ ቆንጆች ፡
ሽማግሌች ፡ ልጆች ፡
መድኅንን ፡ ወድሱት ።
፫ ፡ መንፈሱን ፡ ሰብሐ ፡
አጽናኤ ፡ እስራኤል ።
ከአብና ፡ ከወልድ ፡
ሊባርክን ፡ ተልከ ።
ወድሱት ፡ አብን ፡
ወልድን ፡ መንፈስንም ፡
ሥላሴን ፡ ወድሱት ።

ቁ፩

S. T. 4. Am. 113.

፩ ፡ ቅዱስ ፡ ሥላሴ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ።
በአብ ፡ ተፈጥረናል ።
ወልድም ፡ አዳነ ፡ ሁሉን ፡ ሰው ።
መንፈስ ፡ ይቀድሰናል ።
አብን ፡ ወልድን ፡ መንፈስንም ፡
እናምልክ ፡ እናመስግንም ፡
ካሁን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ረስቲን ።

ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡

ቁ፪

S. T. 50. Am. 155

፩ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡
ምስጋና ፡ ይሁንለት ።
ሕዝቡን ፡ ጐብኝትዋል ፡
በክንዱ ፡ ለመሸከም ።
አድንዋቸዋል ፡

የመድኃኒትም ፡ ቀንድ ፡
እርሱ ፡ አስነሣልን ፡
ዛሬ ፡ በዳዊት ፡ ግንብ ።
፪ ፡ ከጥንትም ፡ ጀምሮ ፡
ለነበሩት ፡ ብፁዓን ፡
በነቢያቱ ፡ አፍ ፡
እንደ ፡ ተወራልን ።
ከጠላቶቻችን ፡
ፍጹም ፡ ሊያድነን ፡
ሊሰጠን ፡ ምሕረት ፡
በጸጋው ፡ ትሩፋት ።
፫ ፡ ከአባቶች ፡ ጋራ ፡
ያደረገው ፡ ኪዳኑ ፡
ሥርዓቱን ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡
መሐላውን ፡ ሊያጸና ።
ለአብርሃም ፡ ያለውን ፡
ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ መዳንን ፡
ፍጹም ፡ ሊያድነን ፡
ከጠላቶቻችን ።

፬ ፡ አውን ፡ ያለ ፡ ፍርሃት ፡
በእውነት ፡ በቅንነት ፡
በፊቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡
እርሱን ፡ ልናገለግል ።
አንተ ፡ ሕፃንም ፡ ሆይ ፡
የልዑል ፡ ነቢይ ፡ ሆይ ፡
መንገዱን ፡ ትጠርግ ፡ ዘንድ ፡
በፊቱ ፡ ልትሔድ ።

፭ ፡ እግሮቻችንን ፡
በቅን ፡ መንገድ ፡ ሊመራ ፡
እኛንም ፡ ባሰበን ፡
ብርሃንም ፡ ባወጣልን ፡
በአምላክ ፡ ምሕረት ፡
ለኃጢአት ፡ ስርየት ፡
የደኅንነት ፡ ዕውቀት ፡
ለሕዝቡ ፡ ልትሰዋ ።

ሉንዳል ፡ B.V.

ጽጌ

S. T. 586.

ማቴ. ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።

፩ ፤ አልመለስ ፡ ብለው ፡ አይሁድ ፡
ሥራውን ፡ ቢቃወሙት ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፡ የሱስ ፡
የዓለሙ ፡ መድኃኒት ፡
ይህችንም ፡ ዘማ ፡ ትውልድ ፡
የአይሁዶችንም ፡ ቤት ፡
ከቶ ፡ በምን ፡ ይሆን ፡ እሷን ፡
ምሳሌ ፡ የማደርጋት ።

፪ ፡ በውነት ፡ እርሷም ፡ ትመስላለች ፡
ዋዘኞች ፡ ሕፃናትን ፡
በገቢያ ፡ መሃል ፡ ቁመው ፡
ዘፈን ፡ የሚዘፍኑትን ፡
በሜዳ ፡ ሰብስበው ፡ ያሉ ፡
ጓደኞቻቸውን ፡
እንደዚህም ፡ የሚሉትን ፡

በዚያ ፡ ተቀማጮችን ፡
፫ ፤ ቀናቀንላችሁ ፡ እኛ ፡
አልዘፈናችሁምም ፡
አስለቀስንላችሁ ፡ ደግሞ ፡
አላለቀሳችሁም ።
ዮሐንስ ፡ መጥቶ ፡ ቢያስተምር ፡
ሳይጠጣና ፡ ሳይበላ ፤
ጋኔን ፡ አለው ፡ አሉት ፡ ደግሞ ፡
እህልን ፡ የሚያስጠላ ።
፬ ፤ እህል ፡ እየበላ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡
ቢያስተምር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
እነሆ ፡ ይሉት ፡ ጀመሩ ፤
የቀራጮች ፡ ወዳጅ ።
የሱስም ፡ እኒያን ፡ አገሮች ፡
ነቀፋቸው ፡ በልቡ ፡
የሚበዛ ፡ ኃይልን ፡ አይተው ፡
ንስሓ ፡ ስላልገቡ ።

The Sweetest Name
S.S. 108

ቁጥ ፬

Am. 90. S. T. 36.

ማቴ. ፲፩ ፡ ፪—፯ ።

፩ ፤ የ·ሐንስ ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ሁኖ ፡
ቢናፍቅ ፡ የሱስን ፡
ቶሎ ፡ ላካቸው ፡ አፋጥኖ ፡
ደቀ ፡ መዛሙርቱን ።
የናፍቆቱም ፡ መልእክት ፡ የርሱ ፡
እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ፡
ትመጣለህ ፡ ብለን ፡ እኛ ፡
የምንጠብቀው ፡
፪ ፤ ከቶ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ይሆን ፡
ወይስ ፡ ሌላ ፡ ነው ፤
ጌታም ፡ ላከበት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡
እንዳይጠራጠር ።
ዕውሮችም ፡ ነጻ ፡ ወጡ ፡
ከጨለማ ፡ ቀንበር ፤
አንካሶችም ፡ ቁመው ፡ ሔዱ ፡
ከፈቀዱት ፡ አገር ፡

፫ ፤ ለምባሞችም ፡ ቆሎ ፡ ነጹ ።
ከርሱሰታቸው ፡ ነውር ፡
መታንም ፡ ደግሞ ፡ ተነሡ ፡
ከወህኒ ፡ መቃብር ።
ለችጋረኞችም ፡ ሁሉ ፡
ወንጌልን ፡ ይሰበክል ፡
ምስጉን ፡ ነው ፡ ያ ፡ ሰው ፡ በእኔ ፡
የማይሰናከል ።

ቁ. ፩.

ቅዱሳን ።

ግእዙ

S. T. 241.

፩ ፤ በየሱስ ፡ ፊት ፡ ይቆማሉ ።
ታላቅ ፡ ወገን ፡
ከሕዝቦች ፡ የተለቀመ ፡
አእላፋት ፡ ቅዱሳን ።
፪ ፤ ነጭ ፡ ልብስን ፡ ለብሰው ፡
ዘምባባን ፡ በእጅ ፡ ጨብጠው ፡

ክፍ ፡ አድርገው ፡ ድምፃቸውን ፡
ጮኹ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡
፫ ፤ መድኃኒት ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡
ለሚቀመጥ ፡
ለአምላካችን ፡ በሰማይ ፡
ምስጋናን ፡ ልንሰጥ ።
፬ ፤ መላእክትም ፡ ቁመው ፡ በዙያ ፡
ከሽማግሌች ፡
ካራትም ፡ እንስሶች ፡ ዙርያ ፡
የሰማያት ፡ ጭፍሮች ።
፭ ፤ በግምባራቸው ፡ ወደቁ ፡
ሊሰግዱ ።
ለልዑል ፡ አምላክ ፡ ለበጉ ፡
ስብሓት ፡ ይሁን ፡ ሲሉ ።
፮ ፤ ግርማና ፡ ክብር ፡ ጥበብም ፡
ላንተ ፡ ይሁን ።
ምስጋና ፡ ኃይልም ፡ ችሎትም ፡
ይገባሃል ። አሜን ።

ሶንዳል ።

The Home Over There
S.S. 942
Br. 43

ቁጥር

S. T. 678. Am. 129.

፩ ፡ የከበረ ፡ ቤት ፡ በሰማይ ፡
የተሰጠ ፡ በየሱስ ፡ ጸጋ ፡
ብዙዓንም ፡ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡
ይሰግዳሉ ፡ ለታረደው ፡ በግ ።
በሰማይ ፡ በሰማይ ፡
የከበረ ፡ ቤት ፡ በሰማይ ፡
በሰማይ ፡ በሰማይ ፡
የከበረ ፡ ቤት ፡ በሰማይ ።
፪ ፡ ስንት፡ጭፍራ፡ሊኖር፡በሰማይ፡
ከወዳጆች ፡ በፊት ፡ ካረፉ ፡
አሁንም ፡ ሰላምና ፡ ደስታ ፡
ያገኛሉ ፡ በፍቅሩ ፡ ብዛት ።
በሰማይ ፡ . . . . ።
፫ ፡ መድኃኒቴ ፡ በዚያ ፡ ነው ፡
የተወደዱ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡
ስለዚህም ፡ እናፍቃለሁ ፡

ከመድኃኒቴ ፡ ጋራ ፡ ልኖር ።
በሰማይ ፡ . . . . ።
፬ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ልደርሰው ፡
መከራዬ ፡ አሁን ፡ አለቀ ።
ዘመዶቼ ፡ ይጠብቁኛል ፡
በፊቴ ፡ የቀደመውም ።
በሰማይ ፡ . . . . ።

ሶንዳል ። — B.V.

ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ቁጥር

S. T. 54.

፩ ፡ ሥሉጥ ፡ አምላክ ፡ ላንተ ፡
ስብሓት ፡
ይልማ ፡ በኛ ፡ ያንተ ፡ ግዛት ።
ያ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡
በምድር ፡ ይሰፋል ።
ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።

፪ ፣ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ተገናት ፡
በዐለት ፡ ላይ ፡ መሠረታት ።
በፍርድ ፡ እንኳ ፡
ትወጣለች ፡ ነጻ ።
ቅዱስ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።
፫ ፣ ልታቅፍ ፡ ሕዝቦችን ፡ ሁሉ ፡
በየሱስ ፡ ስም ፡ ሊሰግዱ ፡
ሊወድሱ ፡
በደስታ ፡ እያሉ ፡
ቅዱስ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
አምላክ ፡ ጸባኦት ።
፬ ፡ ዙፋንህን ፡ ሊጋርዱ ፡
የድል ፡ መዝሙር ፡ ሊዘምሩ ።
ለሱራፌል ፡
ይመልስ ፡ ኪሩቤል ፡
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡
ልዑል ፡ አምላክ ።

O. E.

ቃሉ ።

ግጥ

S. T. 94. Am. 133.

፩ ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉን ፡ የሚሰሙ ፡
አምላክን ፡ የሚወዱ ፡
ታዘው ፡ ለቅዱስ ፡ ፈቃዱ ፡
ለጌታ ፡ የሚለፉ ፡
በመንፈሱ ፡ የሚመሩ ፡
በውነት ፡ ብፁዓን ፡ ሆኑ ፡
መንግሥቱንም ፡ ሊወርሱ ።
፪ ፣ እምነታቸው ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡
ጠብ ፡ ሁከት ፡ በሚገዛ ።
ፍቅራቸው ፡ ደምቆ ፡ ሊነድድ ፡
ፍቅር ፡ በዓለም ፡ ሰበርድ ።
የተስፋቸውም ፡ መሠረት ፡
ጸንቶአል ፡ እንደ ፡ ዐለት ፡
በሞት ፡ ሆነ ፡ በሕይወት ።
፫ ፡ ድመ-ቅ ፡ ጩራ ፡ ክአብ ፡ ግርማ ፡
ይውረድ ፡ በምድር ፡ ዙሪያ ፡

ተንጀርግጎ ፡ ሊያፈራ ፡
ቸርነት ፡ ሰላም ፡ ደስታ ።
በግርማ ፡ የምታገባ ፡
ይች ፡ ምድር ፡ ትሁን ፡ ለኛ ፡
ሰማያዊ ፡ መግቢያ ።

O. E.

ሽህ

S. T. 4. Am. 113.

፩ ፡ ብርሃን ፡ በሌት ፡ እንደሚዘልቅ ፡
የጌታ ፡ ቃል ፡ ይሰፋል ።
የዓለም ፡ ዘመንም ፡ ሲያልቅ ፡
ዙፋኑ ፡ ይረጋጋል ።
ስሙን ፡ በእምነት ፡ ሲጠሩ ፡
ለአምላክ ፡ ልጅ ፡ ይሰግዳሉ ፡
የምድር ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ።
፪ ፡ ሕፃናት ፡ ያቀርቡለታል ፡
በሞት ፡ ጽላም ፡ ብርሃን ፡ ነው ።
በጭንቅም ፡ ለርሱ ፡ ይጮኻል ፡

በደስታ ፡ ቀን ፡ የረሳው ።
በመከራ ፡ በኃዘንም ፡
ኃይል ፡ አጥቶ ፡ ለሚደክም ፡
ሌላ ፡ ረድኤት ፡ አያገኝም ።
፫ ፡ በሞት ፡ በሕይወት ፡ የሱስ ፡ ሁን ፡
ወትሮ ፡ ባጠገባችን ።
ላክልን ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስህን ፡
በቂሰለ ፡ ልባችን ።
ኃይልን ፡ ስጠን ፡ በድካም ፤
ሞት ፡ ሲደርስብን ፡ በሰላም ፡
አድነን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ።

ረስቲን ።

፮

S. T. 481.

ኢሳ ፡ ፶፬ ፡ ፮ ።

፩ ፡ ወለት ፡ ቢፈርስም ፡ ተራራ ፡
ቢወድቅም ፡
እምነቱ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ነው ።

የኪዳኔም ፡ ጸጋ ፡ ከአንቺ ፡ አይርቅም ፤
እንዲህ ፡ የሚል ሽ ፡ መድኃኒትሽ ፡ ነው ።
፪ ፤ አ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ያን ፡ ቃል ፡
እንዳልረሳ ፡
ተስፋህንም ፡ እንድታመን ፡ እርዳኝ ።
ከመቃብሬም ፡ ከእንቅልፌ ፡ ስነሣ ፡
ያ ፡ ክቡር ፡ ቃልህ ፡ በቤትህ ፡ ያግባኝ ።

አና ፡ ሌና ።

፯፩

S. T. 710. Am.121.

፩ ፤ አምላክ ፡ የፈለገው ፡ ካንተ ፡
በግልጥ ፡ ተነግርዋል ።
ሲገሥፅ ፡ ሲመክር ፡ ላንተ ፡
ጥቅም ፡ ይሆንሃል ።
፪ ፤ በገርነት ፡ በትሕትና ፡
በአምላክ ፡ ቃል ፡ አመን ።
ተግተህ ፡ በቀና ፡ ሕሊና ፡
ፈቃዱንም ፡ ፈጽም ።

፫ ፤ በክርስቶስ ፡ ሁሉ ፡ ይቀናል ፤
በኃይሉ ፡ ብርቱ ፡ ነህ ።
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይረዳሃል ፡
ፍቅሩ ፡ ሊያሞቅህ ።
፬ ፤ በቃሉ ፡ የሚያምኑ ፡
ለጽድቅ ፡ አላቸው ፡ ኃይል ።
በምድር ፡ በሰማይ ፡ በርሱ ፡
ሰላም ፡ ብፁዕ ፡ ዕድል ።
፭ ፤ በአንተ ፡ ነው ፡ የአብ ፡ ሥምረት ፡
የዓለም ፡ ተስፋ ፡ ነህ ።
ትላንት ፡ ዛሬ ፡ ሳትለወጥ ፡
ገና ፡ ትኖራለህ ።

O. E.

፯፪

S. T. 538.

፩ ፤ አ ፡ የሱስ ፡ ቃልህ ፡ ጸንትዋል ፡
መንግሥትህም ፡ አይፈርስም ።
ጠላትህ ፡ ይወረወራል ፡

ወዳምባህ ፡ ግን ፡ አይደርስም ።
እስከ ፡ ዘላለም ፡ እንዳይወድቅ ፡
አንተ ፡ በእውነትና ፡ ጽድቅ ፡
ዙፋንህን ፡ አጸናህ ።

፪ ፡ ለኛ ፡ ግን ፡ ቶሎ ፡ የሚያልቅ ፡
የጠፋም ፡ ይመስለናል ።
መሠረቱም ፡ እንደሚወድቅ ፡
መስሎን ፡ ድንግጥ ፡ ይለናል ።
ይህ ፡ ግን ፡ ኃይልህ ፡ ባይሰማን ፡ ነው ፡
መንግሥትህ ፡ የማይጠፋ ፡ ነው ፡
ቃልህም ፡ ይረጋጋል ።

፫ ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ያንተ ፡ ሥልጣን ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለም ።
ከምድር ፡ ሁሉ ፡ ክቡራን ፡
የሚሰግድልህ ፡ የለም ።
የክርስቲያኖችህ ፡ ድካም ፡
ሲታይ ፡ የመንግሥትህ ፡ ሰላም ፡
ለዓለም ፡ ሰው ፡ አይታይም ።

፬ ፡ ተመስገን ፡ ርኅሩኅ ፡ መድኃኔ ፡
ለኔ ፡ ተገለጠልኝ ።
የመንግሥትህ ፡ ወራሽ ፡ ሁኜ ፡
ብዕዕናህ ፡ ደረሰልኝ ።
ከአንተም ፡ ዘንድ ፡ ምስጋናህን ፡
ስዘምር ፡ ታላቅ ፡ ጸጋህን ፡
ዘላለሙ ፡ ላመስግን ።

ረስቲን ።

፮ቮ

S. T. 88.

፩ ፡ አንተ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡
የሚያውቅህ ፡ ብፁዕ ፡ ሆነ ።
ልጅህ ፡ እርሱም ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡
ካንተ ፡ ጋር ፡ አስታረቀን ።
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ሆንህልን ፡
መንገድ ፡ እውነትም ፡ ሕይወትም ።
ለመድኃኒት ፡ የሚሆንን ፡
ሌላ ፡ ስም ፡ ግን ፡ አልተሰጠም ።

ረስቲን ።

፺፱

Am. 59.

፩ ፡ አቤቱ ፡ በጸጋህ ፡
ዓይኔን ፡ ክፈትልኝ ፡
ሕግህን ፡ ሁሉ ፡ አስተምረኝ ።
የአፍህንም ፡ ተአምራት ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡
ሕግህን ፡ ዛሬ ፡ አስተምረኝ ።
ያፍህ ፡ ሕግ ፡ ይሻለኛል ፡
ያፍህ ፡ ሕግ ፡ ይሻለኛል ።
ከአእላፋት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡
ያፍህ ፡ ሕግ ፡ ይሻለኛል ።
፪ ፡ ቃልህ ፡ ሲገለጥ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡
ያፍህን ፡ ሕግ ፡ አስተምረኝ ።
የወሃንንም ፡ አዋቆች ፡ ያደርጋል ፡
ሕግህን ፡ ዛሬ ፡ አስተምረኝ ።
ያፍህ ፡ ሕግ ፡ . . .
፫ ፡ የምስክርህ ፡ ጽድቅ ፡
ለዘላለም ፡ ናት ፡
ሕግህን ፡ ሁሉ ፡ አስተምረኝ ።

እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፡ እድን
ማለሁ ፡
ሕግህን ፡ ዛሬ ፡ አስተምረኝ ።
ያፍህ ፡ ሕግ ፡ . . . ።

R. F. I.

ጥምቀት ።

፺፰

S. T. 112. Am. 135.

፩ ፡ የየሱስ ፡ ስም ፡ ያጸናናል ፡
በመከራም ፡ ይረዳናል ።
በየሱስ ፡ ጸጋ ፡ አለን ፤
የአብን ፡ ሥምረት ፡ ሰጠን ።
፪ ፡ አ ፡ ያምላክ ፡ ልጅ ፡ አ ፡ ረጃችን ፤
በምሕረትህ ፡ ይቅር ፡ በለን ።
ሰው ፡ ነህ ፡ በእውነት ፡ አምላክም ።
እይ ፡ ቁንቃችንን ፡ እርዳንም ።
፫ ፡ ጽድቅ ፡ ሁሉ ፡ ካንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ሰላምም ፡ ዕርቅም ፡ ካንተ ፡ ነው ።

በቅዱስ ፡ ስምህ ፡ ያመነ ፡
እርሱ ፡ ከሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ዳነ ።
፬ ፤ ምስጋና ፡ ስለ ፡ ጥምቀትህ ፡
ስለ ፡ ቅዱርባንም ፡ እንስጥህ ።
በዚህ ፡ ሕይወት ፡ ሰላም ፡ ስጠን ፡
ወደ ፡ ሰማይም ፡ ሰብስበን ።

ረስቲን ።

ጀ፮

S. T. 258.

፩ ፤ የሱስ ፡ ሆይ ፡ ሕማናትን ፡
በቅፍህ ፡ ውስጥ ፡ ተቀበልሃቸው ።
እኛም ፡ ቅዱስ ፡ ተስፋህን ፡
አምነን ፡ ስናቀርባቸው ፡
ባንተም ፡ ስም ፡ ስናጠምቃቸው ፡
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ተቀበላቸው ።
፪ ፤ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያንተ ፡ ደም ፡
በአብ ፡ ፊት ፡ ይቀድሳቸው ።
መንፈስህ ፡ በእምነትም ፡

ሕንተ ፡ ጋር ፡ ያሳብራቸው ።
ምሉ ፡ ጽድቅህን ፡ ይልበሱ ፡
መንግሥትህንም ፡ ይውረሱ ።
፫ ፤ ታናጆቹ ፡ በጎችህ ፡
በረኛቸው ፡ እጅ ፡ ይሁኑ ።
ሰርክ ፡ ዘጠባብ ፡ መንገድህ ፡
ሐደው ፡ ክለም ፡ ሽር ፡ ይዳኑ ።
ርስትህ ፡ እንዳይጠፋብቸው ፤
የሱስ ፡ ሆይ ፤ ና ፡ ጠብቃቸው ።

ረስቲን ።

ጀ፯

Am. 121. S. T. 710.

ዮሐ ፫ ፡ ፭ ።

፩ ፤ ክመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከውኃ ፡
ክልተወለድህ ፡ ዳግም ፡
የአምላክን ፡ መንግሥት ፡ ገብተህ ፡
ልታይ ፡ አትችልም ።
፪ ፤ ለአንተ ፡ እንሰግዳለን ፡
በትሕትና ፡ መንፈስ ፡

ስትጠመቅ ፡ ገብተህ ፡ አንተ ፡
በማየ ፡ ዮርዳኖስ ።

፫ ፤ ልትጠመቅ ፡ አንት ፡ ስትሔድ ፡
በዮሐንስ ፡ እጂ ፡
እርሱም ፡ አለ ፤ ካንት ፡ ልጠመቅ ፡
እኔ ፡ እሻለሁ ፡ እንጂ ።

፬ ፤ አንት ፡ አጥምቀኝ ፡
አለው ፡ ጌታም ፡
ጽድቅን ፡ ለመፈጸም ፡
ለሕዝብም ፡ እንዲሆን ፡ ሕይወት ፡
እስከ ፡ ዘለዓለም ።

፭ ፤ ጌታችን ፡ ሲጠመቅ ፡ በውኃ ፡
ከድንግል ፡ ተወልዶ ፡
በነጭ ፡ ርግብ ፡ አምሳል ፡ ታየ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወርዶ ።

፮ ፤ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ተጠምቆ ፡
ከውኃው ፡ ሲወጣ ፡
እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከሰማይ ፡
በደመና ፡ መጣ ፡

፯ ፤ ይህ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የሰደድሁት ፡
የምወደው ፡ ልጄ ፡
በደሙ ፡ ዓለምን ፡ ሊያድን ፡
እንዲሞት ፡ ወድጄ ።

ቁ. ባ. ደ.

ቅዱስ ፡ ቁርባን ።

S. T. 263.

፩ ፤ አ ፡ የሱስ ፡ ያንተን ፡ ልጆች ፡
መሰብሰብ ፡ ወደድህ ፤
ከመረረው ፡ ሥቃይህ ፡
ብፁዕ ፡ ፍሬ ፡ ለመስጠት ።
እስከ ፡ መሞት ፡ አፈቀርኸን ፡
ወዳባትህም ፡ መንግሥት ፡
ልታገባን ፡ ነው ።

፪ ፤ ወደ ፡ ተማሮችህ ፡ ገና ፡
መምጣት ፡ ትወዳለህ ፤
ያምላክ ፡ መሥዋዕት ፡ ሆንህልን ፡
ሥጋህን ፡ ቈረስህ ።

ውስጡ ፡ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡
እንዲሁም ፡ ደሜን ፡ ጠጡ ፡
ለናንት ፡ ተሰጥቷዋል ።
ቮ ፤ አንተን ፡ እንሰማለን ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ፀልይ ።
ወዳንተ ፡ እንቀርባለን ፡
ወደ ፡ ቅዱስ ፡ እራት ።
ስርየት ፡ ለኃጢአተኞች ፡
በደምህ ፡ ትሰጣለህ ፡
ጌታ ፤ ተቀበለን ።
ፀ ፤ ልብህ ፡ በትግራችን ።
መጠጊያችን ፡ ነው ፡
ፍርዳችንን ፡ በመስቀል ፡
አንተ ፡ ተሸክመኸው ።
አሁን ፡ ሕይወትና ፡ ሰላም ፤
ክአርያምም ፡ ብዕዕና ፡
ለኛ ፡ አካፍለን ።
ፌ ፡ አ ፡ መድኅን ፤ ትመጣለህ ፡
ገና ፡ በፍቅርህ ፤

ወዳጳት ፡ ታደርሳለህ ፡
የጠፋብህን ፡ ልጅ ።
ለዋጀሃቸው ፡ ልጆችህ ፡
ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ለሆኑ ፡
ይቅርታን ፡ ሰጥተሃል ።
ጌ ፤ ላንተ ፡ እንሆናለን ፤
አ ፡ የሱስ ፤ እስከ ፡ ሞት ፤
ፈቃድህን ፡ ለማድረግ ፡
በመንፈስህ ፡ እርዳን ።
ከእኛ ፡ ጋር ፡ ሁን ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡
እስከ ፡ ፍጻሜያችን ፡
እንደ ፡ ክቡር ፡ ተስፋህ ።

ኤዲት ።

፻፲

S. T. 112. Am. 135.

ጌ ፤ የክርስቶስ ፡ ያምላካችን ፡ ሞት ፡
ለመንፈሳችን ፡ ነው ፡ ሕይወት ።
ለልቦናችንም ፡ ሰላም ፡
አግኝተናል ፡ በርሱ ፡ ሕማም ።

፱ ፤ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ከፈሰሰ ፡
ዕዳችን ፡ ተደመሰሰ ።
አጥብቆ ፡ ስለወደደን ፡
ከአምላክ ፡ ጋር ፡ አስታረቀን ።

፲ ፤ ይህንን ፡ እንድናምነው ፡
ጸጋውን ፡ እንድንቀበለው ፡
ቅዱስ ፡ መያዣ ፡ ሰጥቶናል ፡
ቍርበኑንም ፡ ሠርቶልናል ።

፲፩ ፤ አሁን ፡ ሥጋውን ፡ ያበላናል ፤
በማዕዱም ፡ ያጠጣናል ።
ያንን ፡ የፈሰሰልን ፡ ደም ፡
ይሰጣል ፡ ጽድቁንም ።

፲፪ ፤ ይህ ፡ ሰማያዊ ፡ መና ፡ ነው ፤
ይህ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።
ያን ፡ ኅብስት ፡ ስንቀበልም ፡
ዘላለም ፡ አያልቅብንም ።

፫

S. T. 269. 8. Am. 155.

፩ ፤ አ ፡ የሱስ ፡ ጌታዬ ፤
አመሰግንሃለሁ ፤
እራትህ ፡ ለምግቤ ፡
አሁን ፡ ስለ ፡ አገኘሁ ።
ነፍሴን ፡ ስታጠጣ ፡ በከበረ ፡ ደምህ፡
ለልቤ ፡ ተሰጠ ፡ መጽናኛት ፡ ከፍቅርህ ።

፪ ፤ የኃጢአቴን ፡ ሸክም ፡
አሁን ፡ አስወገድህልኝ ፤
በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ጽድቅን ፡
ለግሰህ ፡ አቀረብህልኝ ።
ለሃይማኖቴ ፡ ኃይል ፡
ከንተ ፡ ተቀበልሁ ፤
ከመንፈሴ ፡ ድካም ፡ ዕረፍት ፡ አገኘሁ ።

፫ ፤ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤
የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ነህና ፤
እኔ ፡ ገንዘብህ ፡ ነኝ ፤

ልኖር ፡ ላንተ ፡ ምስጋና ።
ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ኑር ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ቀን ፡
ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ አሻግረኝ ።
አሜን ።

ሉንዳል ።

ደፀ

S. T. 269. 8. Am. 155.

፩ ፤ አ ፡ ቸር ፡ መድኃኒቴ ፤
አንተን ፡ እንዴት ፡ ላመሰግን ፤
በቅዱስ ፡ ምሥጢርህ ፡
አበላኸኝ ፡ ሥጋህን ።
ለልቤም ፡ አዲስ ፡ ኃይል ፡
ከደምህ ፡ ሰጠኸኝ ፡
ካንተ ፡ ተባብሬ ፡
በጸጋህ ፡ ብፁዕ ፡ ነኝ ።
፪ ፤ የኃጢአቴን ፡ ፍርድ ፤
ከኔ ፡ አነሣህልኝ ፡
ወደኔም ፡ መጥተህ ፡

በፍቅርህ ፡ ታየህልኝ ።
ደካማ ፡ እምነቴን ፡
በጸጋህ ፡ ጨመርኸው ፡
በመስቀልህም ፡ ኃይል ፡
ነፍሴን ፡ አጸናኸው ።
፫ ፤ ገንዘብህ ፡ እንድሆን ፡
በመስቀል ፡ የሞትህልኝ ፤
አ ፡ ግሩም ፡ መድኃኒቴ ፤
የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ሆንህልኝ ።
ብፅዕናን ፡ እንድወርስ ፡
ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ቆይ ።
አንተ ፡ ነህ ፡ ሕይወቴ ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ።

ረስቲን ።

የጉባኤ ፡ ስብሰባ ።

ደፀ

S. T. 346.

፩ ፤ በአምላክ ፡ ተመርተን ፡
በቃሉ ፡ ብርሃን ፡

በልጁም ፡ ሲጸና ፡ የምሕረት ፡ ኪዳን ፤
ያላየነው ፡ ዘመን ፡ ሲብት ፡ አንፍራ ።
ያ ፡ ቸር ፡ እረኛችን ፡
ሲኖር ፡ በቅርባችን ፡
ሲሔድ ፡ በፊታችን ፡
ከምን ፡ እንፍራ ፤

፪ ፤ ከጨለማ ፡ ዓለም ፡
ከምድር ፡ ሥቃይ ፡
አንድ ፡ ጭፍራ ፡ ተነሣ ፡ ሊጓዝ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
የጭፍራውም ፡ ገናነት ፡ ተሰውርዋል ፤
ግን ፡ አምላክ ፡ ሲቀድም ፡
ሲከተል ፡ ሲከብም ፡
ሲደግፍ ፡ ሲሸከም ፡
ይጋርደዋል ።

፫ ፤ ከንቱነቱን ፡ ዓለም ፡
ሲፈልግ ፡ ሲሻው ፡
በርኩሰትም ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ደስታው ፤
ያን ፡ ጭፍራ ፡ ልከተል ፡ ሲሔድ ፡

ወደ ፡ ላይ ።
ያልታወቀውን ፡ ክብር ፡
ያልታሰበውን ፡ ነገር ፡
የተስፋውንም ፡ ምድር ፡
ላገኝ ፡ በሰማይ ።

፬ ፤ የደመና ፡ ዓምድ ፡
የእሳት ፡ ግለትም ፡
ውኃ ፡ የሚሰጠን ፡ ሕያው ፡ አለትም ፡
ዘወትር ፡ ሊመሩ ፡ ይከተሉናል ።
ያን ፡ ቅዱስም ፡ አለት ፡
ብታየው ፡ በእምነት ፡
ለሞቱቱ ፡ ሕይወት ፡
ሊሰዋ ፡ ይችላል ።

፭ ፤ ያ ፡ አለትም ፡ ክርስቶስ ፡
መድኃኒቱ ፡ ነው ፤
ያነጻንም ፡ ደም ፡ የወጣበት ፡ ውኃው ።
የኃጢአታችን ፡ ስርየት ፡ አለን ፡
በአንዱ ፡ በየሱስ ።

ያ ፡ ጻድቅ ፡ ያ ፡ ቅዱስ ፡
ለምስኪን ፡ ለርኩስ ፡
መድኃኒት ፡ ሆነ ።
፮ ፡ በሰይጣን ፡ ስጠነቅ ፡
ሲበዛብኝ ፡ ድካም ፡
መድኃኒቴ ፡ ሆነ ፡ የልቤ ፡ ሰላም ።
በመስቀሉ ፡ ሞተ ፡ ለሁሉ ፡ ኃጥአን።
ለሁሉም ፡ ከሞተ ፡
ሁላችንም ፡ ሞትን ፡
ለሁሉም ፡ ከሞተ ፡
ተገኘ ፡ መዳን ።
፯ ፡ በአምላኬ ፡ ፈት ፡
በደለኛ ፡ ስሆን ፡
በየሱስ ፡ ብገኝ ፡ ማን ፡ ይከሰኝ ፡ ይሆን ፡
በየሱስ ፡ በልጁ ፡ የጸደቅሁ ፡ ነኝ ።
በእርሱም ፡ ሲያየኝ ፡
አንድ ፡ ርኩሰትም ፡ የለኝ ፡
ሥምረቱ ፡ ግን ፡ አለኝ ፡
በየሱስ ፡ ስገኝ ።

፰ ፡ ይህም ፡ የብዕዕና ፡
መያዣዬ ፡ ነው ።
የየሱስም ፡ ጽድቅ ፡ መጽናናቴ ፡ ነው ፡
ያነገብሁት ፡ ጋሻም ፡ የደፋሁት ፡ ቀኖር።
መድኃኒቴ ፡ ሳለ ፡
ረድኤት ፡ ዘወትር ፡ አለ ።
መድኃኒቴ ፡ ሳለ ፡
በተስፋ ፡ ልኑር ።
፱ ፡ አ ፡ የሱስ ፡ ያልተውኸን ፡
እስከ ፡ አሁን ፡
መታመንህ ፡ ብቻ ፡ ተስፋችን ፡ ይሁን ።
ተሸከመን ፡ ጋርደን ፡ ከኛም ፡
ዘንድ ፡ ሁን ።
አሜን ፡ ለዘላለም ፡
ምስጋና ፡ ስብሓትም ፡
ለአምላክ ፡ ለበጉም ፡
ሳይጨረስ ፡ ይሁን ።

My God I have found
S.S. 103

፻፫

Am. 33.

፩ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡
ልጁን ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፡
በክቡር ፡ደሙም ፡ደግሞ ፡ ስለ ፡ ገዛን።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አሜን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡
ባርከነ ፡ አሁን ።
፪ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡
መንፈስ ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፡
ከፈለማም ፡ወደ ፡ብርሃን ፡ ስለ ፡ጠራን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡ . . . .
፫ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡
ለክርስቶስ ፡ ይሁን ፡
ኃጢአታችንም ፡ ስለ ፡ ተሸከመልን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡ . . . .
፬ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡
ላምላካችን ፡ ይሁን ፡

አንድ ፡ልጁንም ፡አሳልፎ ፡ ስለ ፡ሰጠን።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡ . . . .
፭ ፡ ባርከነ ፡ አሁን ፡
ፍቅርህን ፡ አካፍለን ፡
አንድነታችንንም ፡ አካፍልልነ ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይመስገን ፡ . . . .

፻፹

Am. 187.

፩ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡
በመቅደሱ ፡ ይመስገን ፡
ኑ ፡ አምላክን ፡ እናመስግን ፡
በመልካም ፡ ድምፅ ፡ ጩኸን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ እናመስግን ፡
በችሎቱ ፡ ይመስገን ፡
እንደ ፡ ታላቅነቱ ፡ ይሁን ፡
ስንወድስ ፡ አምላክን ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡
ሕይወት ፡ ያለው ፡ ያመስግን ፡

በመልካም ፡ ድምጽ ፡ ያመስግን ፡
ያቅርብለትም ፡ ውዳሴን ፡
በመልካም ፡ ድምጽ ፡ ያመስግን ፡
ያቅርብለት ፡ ውዳሴን ።
ፀ ፡ ኑ ፡ አምላክን ፡ እናመስግን ፡
በከበሮና ፡ ዘፈን ፡
እንደ ፡ ታላቅነቱ ፡ መጠን ፡
በእንቢልታ ፡ ይመስገን ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ እናመስግን ፡
በመሰንቆ ፡ አድርገን ፡
እናመስግን ፡ ጌታችንን ፡
እናክብረው ፡ አምላክን ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡

ደ፩

S. T. 12. Am. 66.

፩ ፡ አ ቅዱስ ፡ አባት ፡
አሁን ፡ ቅረበን ፡
ከቅዱስ ፡ ታልህ ፡ ና ፡ አቅምሰን ።

ከልመናችን ፡ አብልጠህ ፡ ስጠን ።
አምላክ ፡ ስማን ።
፪ ፡ ሁን ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡
የሱስ ፡ የሞትህልን ።
በጭንቀት፡እርዳን፡ስንጮኽ፡ስግልን።
ተሸከመን ፡ ደክመን ፡ ስንጣምን ፡
አንተ ፡ ኃይላችን ።
፫ ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡
እውነትን ፡ አሳየን ፡
የሰማይ፡ርግብ፡አሁን፡ይውረድልን፡
ቀድሰህ፡ባርከው፡ሁሉን፡የሚለምን ።
አሜን ፡ ይሁንን ።

O. E

ደ፯

S. T. 23. Am. 132.

፩ ፡ ታልህን ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ ጌታ ፡
ልንሰማ ፡ ሰብስበን ።
በልባችን ፡ እንዳዝመራ ፡

ሊዘንብልን ፡ ባርከን ።
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስጠን ፡
ጸጋህንም ፡ ግለጥልን ፡
ይርበናል ፡ አቅምሰን ፡
አ ፡ ጌታችን ፡ ቃልህን ።
ፂ ፡ ቃልህንም ፡ ስትሰጠን ፡
ልንቀበለው ፡ እርዳን ።
በብርሃንህም ፡ አብራልን ፤
በቅን ፡ መንገድም ፡ ምራን ።
ከለማመን ፡ ጠብቀን ፡
ከድንዛዜም ፡ አድነን ።
ጸጋህም ፡ እንዳይቀርብን ፡
ባርክልን ፡ ቃልህን ።
ቮ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል ፡ ዘመናችን ፡
አንተ ፡ ስትፈልገን ።
ጸጋህን ፡ እንዳናባክን ፡
አምላክ ፡ ሆይ ፡ አሳስበን ።
ዛሬ ፡ ስትናገረን ፡

ለመስማት ፡ አስተምረን ፡
የልብ ፡ ጆሮን ፡ ክፈትልን ፡
አሰማነ ፡ ቃልህን ።

ጸጋ

S. T. 11.

፩ ፡ ቸር ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡
በመቅደስህ ፡
መሰብሰብ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።
በዚህ ፡ ይታያል ፡ ክብረትህ ፡
መልካም ፡ ድምፅህ ፡ ይሰማል ።
በመዝሙር ፡ ወይ ፡ በቅዳሴ ፡
በስብከት ፡ በጸሎት ፡ ልቤ ፡
ከአምላክ ፡ ይተባበር ።
፪ ፡ ከዓለም ፡ ደስታ ፡ ይልቅ ፡
ካንተ ፡ መዋል ፡ ይበልጣል ።
ከቅዱስ ፡ ቤትህ ፡ የሚርቅ ፡
ድኃ ፡ ሁኖ ፡ ይቀራል ።
ምሉ ፡ ደስታን ፡ ትሰጣለህ ፡

ለሁላችን ፡ በመቅደስህ ፡
ምሕረትህ ፡ በሚገለጥ ።
፫ ፡ ሕይወትን ፡ ኃይልንም ፡
አውርደህ ፡
በቃልህ ፡ አጸናናህ ።
የለመኑትን ፡ ባርከህ ፡
ነፍሳቸውንም ፡ አርክ ።
መቅደስህ ፡ በዘ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ እድሞ ፡ ነው ፡ ለሰማይ ፡
ብዕዕና ፡ የሞላበት ።
፬ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ላክልን ፡
ቅን ፡ መንገድ ፡ የሚመራ ፡
በጽድቁ ፡ የሚያድሰን ፡
ኃይልን ፡ የሚያጸና ።
ያን ፡ ቅዱስ ፡ ቃልህን ፡ ለመስማት ፡
ለማድረግም ፡ ደግሞ ፡ ትጋት ፡
ጌታ ፤ አካፍለን ።
፭ ፡ አ ፡ አብ ፡ ላንተ ፡ ስብሐት ፡ ይሁን ፡

አ ፡ የሱስ ፡ ወልድ ፤ ተመስገን ።
አ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አጽናኝ ፡
ስማ ፡ ውዳሴያችን ።
ከለቀቅን ፡ ከዚች ፡ ዓለም ፤
በመቅደስህ ፡ ለዘላለም ፡
ብዕዕናን ፡ ስጠን ። አሜን ።

O. E.

ጀሮ

S. T. 215. Am.182.

፩ ፡ ንብተናል ፡ በአምላክ ፡ መቅደስ ፡
ግርማውን ፡ በሚያሳይ ።
እንስገድ ፡ በቀና ፡ መንፈስ ፡
ላባታችን ፡ በሰማይ ።
ጸሎታችንን ፡ ይሰማል ፤
ጸጋን ፡ ምሕረትን ፡ ይሰጣል ።
፪ ፡ ስመጣ ፡ ወዳንተ ፡ እኔን ፤
ቸር ፡ አባት ፡ ተቀበለኝ ።
መቅደስህ ፡ ይሁን ፡ በልቤ ፡

ከክፋቱ ፡ አንጻልኝ ።
አስርጽበት ፡ ቅድስና ፡
ምላበት ፡ ያንተን ፡ ብዕዕና ።
፫ ፡ ልቤን፡አድርግ፡ፍሬያም፡እርሻ፡
ቅዱስ ፡ ዘር ፡ ሲዘራበት ።
ጨለማን ፡ ከልቤ ፡ አጥፋ ፡
ስጥ ፡ በስብከት ፡ በረከት ።
በመስማቱ ፡ ከበንነት ፡
ፍሬን ፡ ላፈራ ፡ ላንተ ፡ ክብረት ።
፬ ፡ እሰማለሁ ፡ ጌታ ፡ እዘዝ ፡
ትእዛዝህ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።
የሕይወት ፡ ውኃ ፡ ሲፈስስ ፡
የማይረካ ፡ ይጠፋል ።
መግበን ፡ በቸርነት ፡
አድነን ፡ ከሁሉ ፡ ጭንቀት ።

O. E

ፕ፱

S. T. 793. Am. 91.

፩ ፡ ከአምላክ፡ዘንድ፡በመገናኘት ፡
ልብህ ፡ ይታደል ፡ በረከት ።

ተለይተህ ፡ ከዓለምም ፡ ሁከት ፡
ልብ ፡ ይቀምሳል ፡ ሰላም ፡ ዕረፍት።
ያምላክ ፡ ተድላ ፡ ይጥመዋል ፡
በምሕረቱ ፡ ይታደላል ።
፪ ፡ ምስጉን፡እርሱ፡በቃል፡በሥራ ፡
በአምላክ ፡ ሕግ ፡ የሚመራ ፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ በቅድስና ፡
አሳቡን ፡ የሚያነሣ ።
ይቀምሳል ፡ በምድር እንኳ ፡
ያምላክን ፡ መንግሥት ፡ ብዕዕና ።
፫ ፡ ምነው ፡ ሰዎች ፡ የሚወራጹ፡
በከንቱ ፡ የሚቃትቱ ፡
እናንት ፡ ብዕዕናን ፡ የምትሹ ፡
ያምላክን ፡ መቅደስ ፡ አትርሱ ።
ያምላክ ፡ ፍቅር ፡ የሠራውን ፡
እንይ ፡ በእምነት ፡ ዓይናችን ።
፬ ፡ ዝገቡ ፡ ሰማያዊ ፡ ገንዘብ ፡
ያ ፡ ሞት ፡ እንኳ ፡ የማይነዝብ ።

በዚህ፡ ነው ፡ መንፈስ፡ የሚጠግብ ፡
የሚሆንለት ፡ ክቡር ፡ ረብ ።
ያምላክን ፡ ወንጌል ፡ መርምሩ ፡
ነዋሪ ፡ ሀብትን ፡ ሰብስቡ ፡

፫ ፡ አ ፡ አምላክ ፡ በሩን ፡
ክፈትልኝ ፡
ወዳንተ ፡ ፍቅር ፡ ውስጥ ፡ አግባኝ፡
በቃልህ ፡ መንገድን ፡ አሳየኝ ፡
በርሱ ፡ ነው ፡ ረድኤት ፡ የሚገኝ ።
አስተርጉምልኝ ፡ ምሥጢሩን ፡
አስገንዝበኝ ፡ ትልቅ ፡ ትርፉን ።

፯ ፡ ሰማይ፡ተከፍቶ፡እምነት፡ያያል፡
በምላክ ፡ ዙፋንም ፡ ይደርሳል ።
ዘወትር ፡ ውርጅብኝ ፡ ይነግል ፡
በምላክ ፡ የጸና ፡ ይቆማል ።
ስኖር ፡ ከአምላኬ ፡ ጋራ ፡
ልቤ ፡ ይመላል ፡ በደስታ ።

O. E

፻፲

S. T. 4. Am. 113.

፩ ፡ አ ፡ መንፈስ፡ሕይወትን፡ላገኝ፡
ነፍሴን ፡ በእውነት ፡ ምራ ።
በሰጠኸኝ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡
ብርሃን ፡ በልቤ ፡ አብራ ፡
በአንተ ፡ ኃይልና ፡ ፍቅር ፡
ተደግፌ ፡ ያንተን ፡ ምክር ፡
በንብረቱ ፡ ላመስገን ።

N. N

፻፲፩

S. T. 462. Am. 142.

፩ የሱስ ፡ ሆይ ፡ ምራን ፡
በቃልህ ፡ ግዛን ።
ተንቅሎ ፡ ሲቀር ፡ ይህ ፡ ድንኳን ፡
ወደ ፡ ሰማያዊ ፡ ከንአን ፡
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ምራን ፡
በሰማይ ፡ አግባን ።

O. E

ጋብቻ ።

ያ፲፱

S. T. 50. Am. 155.

፩ ፡ አምላክ ፡ በመንፈስህ ፡
የሚጋቡን ፡ ምራቸው ።
ወትሮ ፡ ሊኖሩልህ ፡
አጽና ፡ እንድነታቸው ።
ደስታ ፡ ሆነ ፡ ኃዘን ፡
ሁሉ ፡ ፈቃድህን ፡
እያመሰገኑ ፡
ወደው ፡ ሊቀበሉ ።
፪ ፤ አ ፡ አምላክ ፤ ባርከው ፡
የወንድሞችን ፡ ኪዳን ፡
በፍቅር ፡ አመ·ቀው ፡
ስጣቸው ፡ ክቡር ፡ ጸጋን ።
ኪዳን ፡ በሞት ፡ ሲፈርስ ፡
አግባ ፡ ባንተ ፡ ሞገስ ፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ መንግሥት ።
የሚመኙትን ፡ ስጥ ።

ንብረ ፡ ሥላሴ ።

Oh Happy Day
S. S. 866

ያ፲፫ Ave, 98

S. T. 369.

ዮሐ. ፪ ፡ ፩ ።

፩ ፡ ለሠርግ ፡ ሲጠራ ፡ በክብር ፡
ከሐዋርያቱ ፡ ጋር ፡
ደስ ፡ ብሎት ፡ ሐዲ ፡ ጌታም ፡
ከዚያው ፡ ከሠርጉ ፡ መንደር ።
መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡
እርሱ ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ ክብር ።
፪ ፤ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡
የታል ፡ ኪዳን ፡ ሕግ ፡ ወዳጂ ፡
ጥሩውን ፡ ውኃ ፡ ለውጠ ፡
አደረገው ፡ የወይን ፡ ጠጂ ።
ከሰማይ ፡ የመጣልን ፡
እርሱ ፡ ነው ፡ የአምላክ ፡ ልጂ ፡
፫ ፤ ቀምሶ ፡ አደነቀ ፡ በጣም ፡
የተከበረው ፡ ካህን ፡
ለምን ፡ አቆየህ ፡ እስክ ፡ አሁን ፡

ይህን ፡ ያማረውን ፡ ወይን ፡
በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነበር ፡
አስቀድመህ ፡ ብትሰጠን ።

፬ ፡ የቃል ፡ ኪዳንንም ፡ ሥርዓት ፡
ጌታ ፡ በቃሉ ፡ አጸናው ፡
እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡
አሁን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ናቸው ፡
እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞታቸው ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ አይለያቸው ።

፭ ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ሥራት ፡
የሚያፈርስ ፡ ሰው ፡ በኃይል ፡
በአምላካችን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡
ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ ይቀበላል ፡
በሰይጣን ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡
እንዲወርድ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ።

፻፲፬

S. T. 94. 768.

፩ ፡ አምላክ ፡ ሁለቱን ፡ ምሩጣው ፡
ቅድስ ፡ ኪዳናቸውን ።
ደስታ ፡ ኃዘን ፡ ሲቆያቸው ፡
ዘትር ፡ ሁናቸው ፡ ተገን ።
ፍቅርና ፡ ቸርነት ፡
ሰላም ፡ ደስታ ፡ አንድነት ፡
ይደር ፡ በሚጋቡበት ።

፪ ፡ ባንድነት ፡ በሚኖሩበት ፡
ዕድሜያቸውን ፡ አርዝም ።
አቅልል ፡ በልጆች ፡ ደግነት ፡
የእርጅናውን ፡ ሸክም ።
ይሁን ፡ ትጋት ፡ ቅንነት ፡
የሚታገሥ ፡ በጎነት ፡
የቤታቸው ፡ መሠረት ።

፫ ፡ በዓለም ፡ በሚሔዱበት ፡
ምሩጣው ፡ በጉ ፡ ምክር ።
ሊረዳው ፡ በትዕግሥት ፡

ደግፋቸው ፡ በፍቅር ።
ጸጋን ፡ ለርሳቸው ፡ ለግስ ፡
ስጣቸው ፡ ያንተን ፡ ሞገስ ፡
ዕድሜያቸው ፡ እስኪደርስ ።
፬ ፡ ብፁዕ ፡ ደሞዝን ፡ ልታድል ፡
በፍርሃትህ ፡ ቢጸኑ ።
ቢያነሡት ፡ ያንትን ፡ መስቀል ፡
ደስታህን ፡ ሊቀምሱ ።
በተድላ ፡ ወይ ፡ በጭንቀት ፡
በትርፍ ፡ ሆነ ፡ በጕድለት ፡
ይኑሩ ፡ በአንድነት ።
፭ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ሲቈለቈል ፡
ሁለቱ ፡ ሲለያዩ ፡
ሞት ፡ ነጥቆ ፡ አንዱን ፡ ሲነጥል ፡
ጫ ፡ ሲል ፡ በባዶ ፡ ቤቱ ፡
አዘንተኛን ፡ ደስ ፡ አሰኝ ።
ሁለቱን ፡ ሞት ፡ በማይገኝ ፡
ሰብስብ ፡ በሰማይ ፡ እልፍኝ ።

የወንጌል ፡ ሥራ ።

ደ፲፫

S. T. 281. Am. 131.

፩ ፡ የአምላክ ፡ ቃል ፡
ያሸንፋል ፡
የጨለማውን ፡ ቁጥራ ፡
ሰላም ፡ ላጡ ፡
ለወደቁ ፡
ይሰጣል ፡ ጽኑ ፡ ተስፋ ።
፪ ፡ በትእዛዙ ፡
ሰባኮቹ ፡
ወጡ ፡ በመላ ፡ ዓለም ።
ክፉ ፡ ቅናት ፡
ሰይፍ ፡ ወይም ፡ እሳት ፡
ወንጌሉን ፡ አያስቀርም ።
፫ ፡ ለጨካኞች ፡
ላመጸኞች ፡
ጽድቅን ፡ ይሰብካሉ ።
ብጨለማ ፡

እንዲበራ ፡
ብርሃኑን ፡ ያቆማሉ ።
፬ ፡ በዓለሙ ፡
ይዘራሉ ፡
አምላክ ፡ ዘሩን ፡ ያለማል ።
በምሕረት ፡ ቀን ፡
አንድ ፡ ነፍስ ፡ ቢድን ፤
አምላክን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።
፭ ፡ ልዑል ፡ ንጉሥ ፤
በኛ ፡ ንገሥ ፡
ግዛትህንም ፡ አስፋ ።
ድል ፡ ያንተ ፡ ነው ፡
በዓለሙ ።
ላንተ ፡ ይሁን ፡ ምስጋና ።

O. E.

የገጽ

S. T. 620.

፩ ፤ ፀሐይ ፡ ወጣ ፤ አሁን ፡ ንቁ ፤
ድል ፡ ይነሣል ፡ ብርሃኑ ፡

ሕዝቦች ፡ በመንጌል ፡ ሊሰቡ ፤
የሱስን ፡ ሊያመልኩ ።
፪ ፤ አሁን ፡ አምላካዊ ፡ ግርማ ፡
በምድራችን ፡ ላይ ፡ ወጣ ።
ሌት ፡ ሰፈረስ ፡ ቀን ፡ ሰበራ ፡
እናመስገን ፡ በደስታ ።
፫ ፤ አሁን ፡ ንጉሡ ፡ ይመጣል ፤
ሕዝቡንም ፡ ያስከትታል ።
አሕዛብንም ፡ ይጠራል ፤
ከጠፅዕናው ፡ ያድላል ።
፬ ፤ አላንት ፡ ሕዝቦች ፡ አሁን ፡ አዩ ፡
ልጆቻችሁ ፡ ሲመጡ ።
ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሠርግ ፡ ሊገቡ ፡
ነጭ ፡ ሐር ፡ ልብስ ፡ ተጐነቡ ።
፭ ፤ ቄነጃጅታችሁ ፡ ወጡ ፡
ንጉሡን ፡ ሊቀበሉ ።
ሕፃናት ፡ ያከብራሉ ፤
ስለ ፡ ፍቅሩ ፡ ሲሰሙ ።

ጌ ፡ ወድሱት ፡ አምላክ ፡ ይጸናል ፡
በሰጠን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ።
ተክሉን ፡ በምሕረት ፡ ያለማል ።
ዘወትር ፡ ይቆምልናል ።

ጌ ፡ ሥራውን ፡ በእርግጥ ፡ ሊፈጽም ፡
አንድ ፡ እንኳ ፡ አይወዝፍም ።
ግርማውን ፡ ይታይ ፡ በዓለም ፡
የመስገን ፡ ለዘላለም ።

O. E.

ያ፲፮ ፡

S. T. 252.

ፌ ፡ ኃጢአተኞችን ፡ እንዲያድን ፡
መድኃኒታችን ፡ ተልከዋል ።
ያን ፡ ጥልቅ ፡ የአምላክ ፡
ምስጢር ፡ ለማመን ፡
ያን ፡ ቃል ፡ መቀበል ፡ ይገባናል ።

ፍ ፡ አ዁ን ፡ በዓለም ፡ ወንጌል ፡
ይሰፋል ።

መስፋቱን ፡ ማን ፡ ይከለክላል ፡
ያ ፡ ሰማያዊ ፡ አሳት ፡ ይነዳል ፡
ብርሃን ፡ በሌሊት ፡ ይሰጠናል ።

ፎ ፡ በየሱስ ፡ ኃይል ፡ ሰውራን ፡ ያያሉ ፡
የዲዳ ፡ አፍም ፡ ይናገራል ።
በደስታ ፡ ሽቦችም ፡ ይዘላሉ ፡
ከሞት ፡ አልዓዛር ፡ ይመለሳል ።

ፏ ፡ በዚህ ፡ የወደቀውን ፡ ደረቅ
አጥንት ፡
አ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ተመልከተው ።
የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ የሞተውን ፡
አጥንት ፡
ሥጋን ፡ ጅማትንም ፡ ያልብሰው ።

ፐ ፡ ሰማይን ፡ ቀደህ ፡
ወረድህልን ።
አለት ፡ ይሰበር ፡ ድንጋይ ፡ ይቅለጥ ።
በበረሃ ፡ መናን ፡ አውርደህልን ፡
የመስቀልህንም ፡ ኃይል ፡ ግለጥ ።

ጌ ፤ በእግርህ ፡ ታች ፡ አሕዛብ ፡
ይስገዱ ፤
የአልጋህ ፡ ግርማ ፡ በዚህ ፡ ይምላ ።
ከጸጋ ፡ ምንጭ ፡ ሕይወትን ፡ ይውሰዱ ።
ስምህ ፡ ይቀደስ ። ሃሴ ፡ ሉያ ።
እና ፡ ሌና ።

የ፲፰

S. T. 49. Am. 139.

፩ ፤ ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፡ በሚበረከት ፤
ሌሊት ፡ በሚበራበት ፤
ያ ፡ ብሩህ ፡ ቀን ፡ ይምጣ ፡ ለፍጥረት ፤
አውርድልን ፡ በረከት ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስብሓት ፡
ሊነገር ፡ ከአእላፋት ።
፪ ፤ ምሥራቅ ፤ ምዕራብ ፤
ደቡብ ፤ ሰሜን ፡
እስኪደርስ ፡ ግዛትህን ፡
ቶሎ ፡ በወንጌል ፡ አወልጥን ፤

የጥንት ፡ ተስፋን ፡ ምላልን ፤
ዘርህ ፡ እጅግ ፡ ይብዛል ፡
በአንተ ፡ ይባረክል ።
፫ ፤ ልታነድ ፡ የመጣህለት ፡
ቅዱሱን ፡ እሳት ፡ ግለጥ ።
አንቀላቅለው ፡ በእውነት ፤
ብርሃን ፤ መቀት ፡ እንዲሰጥ ።
የጠፉትን ፡ ልንወድ ፡
ፍቅርህን ፡ በኛ ፡ አንድድ ።
፬ ፤ ትሰማለህ ፡ ስንለምን ፤
እንኳ ፡ ቢዘገይብን ።
አሕዛብን ፡ ልታሳምን ፡
የለም ፡ ለርስትህ ፡ ወሰን ።
ጸጋህን ፡ ለምታሳይ ፡
ስብሓት ፡ ላንተ ፡ በሰማይ ።

O. E

የ፲፱

S. T. 148.

፩ ፤ ወንድሞቼ ፤ እንኳ ፤
እንገስግስ ፡ በእልልታ ።

የሱስ ፡ ኄሙ ፡ ክኛ ፡ ጋራ ።
መስቀሉንም ፡ እንሸክም ።
ለመከተል ፡ ብንደክም ፡
ሳይረዳን ፡ አይተወንም ።
በቅን ፡ መንገድ ፡ ይመራናል ፤
ከጉዳት ፡ ይጠብቀናል ።

፪ ፡ የሱስ ፡ ገባ ፡ በጅግንነት ።
ወር ፡ ወደ ፡ ተፋፋመበት ።
እንከተል ፡ በያፍረት ።
በጌታ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡
መ·ተን ፡ ብንራገፍ ፡ እንኳ ፡
ከእውነት ፡ አንዘባ ።
ክብሩም ፡ በኛ ፡ ይንሰራፋ ፤
ይፈጸም ፡ የንጉሥ ፡ ተስፋ ።

፫ ፡ አርበኞች ፡ ሁነን ፡ በፍጥነት ፡
ብንዋጋ ፡ ለመሠረት ፡
በለሙ ፡ ቅዱስ ፡ እውነት ።
የውሸት ፡ ምሽግ ፡ ለፈርስ ፡

ድል ፡ ሁኖ ፡ ክፋት ፡ ለዘለለ ፤
የሱስ ፡ ብቻ ፡ እስኪነግሥ ።
ምሕረቱ ፡ በሚታይበት ፡
ለሰፋ ፡ የመዳን ፡ ዕውቀት ።

፬ ፡ ብርቱ ፡ ጅግና ፡ ሆነ ፡ ስሙ ፤
የተሳለ ፡ ሰይፍም ፡ ቃሉ ፡
ታጠቀ ፡ በእውነቱ ።
በሚገባ ፡ ድል ፡ ይነግል ፤
ሁከት ፡ በሰላም ፡ ይተካል ፤
ሰው ፡ ከጥፋት ፡ ይድናል ።
የሚማቅቅ ፡ በባርነት ፡
በርሱ ፡ ያገኛል ፡ አርነት ።

፭ ፡ አባቶች ፡ አሻግረው ፡ ያዩት ፡
ጻድቃን ፡ በትንቢት ፡ የጻፉት ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለታይ ፡ በግልጥ ።
ሕዝቡ ፡ እየቀለዱበት ፡
የሞቱ ፡ በመስቀል ፡ እንጨት ፡
ንጉሥ ፡ ሁኖ ፡ ለገለጥ ፡

ለማያፍሩ ፡ በመስቀል ፡
ከክብረቱ ፡ ሊያከፍል ።
፮ ፡ ለግዛቱ ፡ እንሰለፍ ፤
በሥራችን ፡ እንወዘፍ ፡
ቀን ፡ በከንቱ ፡ እናሳልፍ ።
ብርሃኑ ፡ በማይጠፋብን ፡
በሰማያዊ ፡ ቤታችን ፡
ሰላም ፡ ዕረፍት ፡ ሊቆየን ።
ስንሻገር ፡ ከዚች ፡ ምድር ፡
እልል ፡ ብለን ፡ እንዘምር ።

O. E.

፻፷

S. T. 12. Am.66.

፩ ፡ አ ፡ የሱስ ፡ አሙቅ ፡
የልቤን ፡ ፍቅር ።
እርዳኝ ፡ ልጋደል ፡ ለአንተ ፡ ክብር።
የወንጌል ፡ መልእክት ፡ ይስፋ ፡
በምድር ፡

መንግሥትህ ፡ ይልማ ።
፪ ፡ የቀና ፡ እምነት ፡ ስጠኝ ፡ ልጋደል ፡
ደግሞም ፡ ልታገሥ ፡ ኃይልህን ፡
ዐድል ።
ድልን ፡ ዕረፍትን ፡ እርዳኝ ፡ ልቀበል ፡
ሩጫን ፡ ስፈጽም ።

N. N
Stand Up
Stand Up
S.S.680

፻፸፩

Am. 20. S. T. 556.

፩ ፡ ንቁ ፡ ቁሙ ፡ ለየሱስ ፡
እናንት ፡ ወታደሩ ፤
የጽድቁን ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፡
በርሱ ፡ ተመሩ ።
ጠላት ፡ ሁሉ ፡ እስኪሸነፍ ፡
እርሱ ፡ ሊረዳችሁ ፡
ከድልም ፡ ወደ ፡ ድልም ፡
በርሱ ፡ ታምናላችሁ ።
፪ ፡ ንቁ ፡ ቁሙ ፡ ለየሱስ ፡
ጌታን ፡ ተመልከቱ ።

ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ ሲታይ ፡
በደመቀ ፡ ፊቱ ፡
ተነሥተን ፡ እንገናኝ ፡
በላይ ፡ በደመና ፡
በእርሱ ፡ ደስ ፡ እንዲለን ፡
አምበችን ፡ ነውና ።

፫ ፡ ንቁ ፡ ቁሙ ፡ ለየሱስ ፡
በብርታቱ ፡ ቁሙ ፡
የሥጋ ፡ ክንድ ፡ አይችልም ፡
በጨለማ ፡ ዓለም ፡
ስለዚህ ፡ ልትድኑ ፡ በፈሰሰው ፡ ደሙ ፡
ወንጌልንም ፡ ልበሱ ፡
ትእዛዙንም ፡ ስሙ ።

፬ ፡ ንቁ ፡ ቁሙ ፡ ለየሱስ ፡
እናንተ ፡ ሎላልቱ ፡
ዛሬ ፡ በዘመቻ ፡ ቀን ፡
ለድላችሁ ፡ በርቱ ፡
ለርሱ ፡ የሚያሸንፍ ፡

ሊኖር ፡ በመንግሥቱ ፡
ተስፋ ፡ ተደርጎለታል ፡
በሰማዩ ፡ ርስቱ ።

ደቂቁ

S. T. 557.

፩ ፡ ለትልቅ ፡ ሥራህ ፡ ሰነፍ ፡ ነኝ ፡
ኃይልን ፡ ጸጋን ፡ ላክልኝ ።
ድካሜ ፡ ኃይልህን ፡ ይግለጥ ፡
ሥራዬ ፡ ያንተን ፡ ክብረት ።

፪ ፡ ፍጠር ፡ በልቤ ፡ ቅን ፡ እምነት ፡
ትሕትናን ፡ አስርጽበት ።
ላከኝ ፡ መስቀልህን ፡ ልተክል ፡
ከጭንቅ ፡ ከሞት ፡ መሀከል ።

፫ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ላንተ ፡ ነኝ ፡
የለም ፡ የሚታጣብኝ ።
ካሁን ፡ ምራኝ ፡ በንተ ፡ ሥምረት ፡
ቁምልኝ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ።

O. E.

መጠራትና ፡ ብርሃን ፡ መቀበል ።

ደሸር

S. T. 272. Am. 93.

፩ ፡ አዲስ ፡ ያልተወለደ ፡
ላዲስ ፡ ሕይወት ፡
ያምላክን ፡ መንግሥት ፡ አያይም ።
ክርስቶስን ፡ ያልያዘ ፡
በልብ ፡ ሃይማኖት ፡
ወደ ፡ ሰማይም ፡ አይገባም ።
ደጁም ፡ ጠባብ ፡ ነው ፤
ተጋደል ፡ ለመግባት ።
ቀንም ፡ አጭር ፡ ነች ፡ እንዳታባክናት ።
ልትጥር ፡ ያስፈልግሃል ፡ በፍርሃት ፡
እንዳይቀርብህ ፡ ብዕዕናው ።
፪ ፡ ሰምተህ ፡ ከመዳን ፡
ይክለክልሃል ፡
ሰይጣን ፤ ያ ፡ ክፉ ፡ ጠላትህ ።
ባለም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያታልልሃል ፡

እንዳትድን ፡ ክጥፋትህ ።
ድምጹን ፡ አትስማ ፡
ፍሬው ፡ ወዳጁ ፡ ሆይ ።
ካለም ፡ ምንጮች ፡ ራቅ ፡
በዚያም ፡ አትቆይ ።
ንስሐ ፡ ለማድረግም ፡ አትዘግይ ፡
የሱስ ፡ በፍቅር ፡ ሰጠራህ ።
፫ ፡ በሰማይ ፡ ለጻርህ ፡ ለትግልህም ፡
ምን ፡ ያህል ፡ ወረታ ፡ አለህ ።
ወዲያም ፡ ከደረስክ ፡ አይጸጽትህም ፤
አክሊልህን ፡ ታገኛለህ ።
ስለዚህ ፡ ተነሥ ፡ አውንም ፡ ተዘጋጅ ።
ይቀርብብሃል ፡ የዓለሙ ፡ ፈራጅ ፤
የሠርግ ፡ ልብስ ፡ ያለበሰው ፡
በሰማይ ፡ ደጅ ፡
አስክ ፡ ዘላለም ፡ አይገባም ።
፬ ፡ እውነተኛ ፡ እምነት ፡
በልብህ ፡ ባይገኝ ፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ አትደርስም ።

የክርስቶስን ፡ ጽድቅ ፡
ልትለብስ ፡ ባትመኝ ፡
ሕይወትንም ፡ አትወርስም ።
ልትድን ፡ ከሆንክ ፡
በእምነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።
የክርስቶስን ፡ ጽድቅ ፡
አውን ፡ ተቀበለው ፡
የሱስም ፡ በፍቅር ፡ ሲጠራህ ፡ ስማው፤
እርሱን ፡ የሰማ ፡ ይድናል ።
ፀ ፡ የሕወትን ፡ ዘውድ ፤
እንዲቁን ፡ ለመጣር ፡
ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ተጠራ ።
ላንተም ፡ ዘውድ ፡ ተዋጀ ፡
በየሱስ ፡ ተግባር ፤
ላንተም ፡ በፍቅሩ ፡ ራራ ።
ታላቁ ፡ መሐሪ ፡ ያዝንልሃል ።
እጁንም ፡ በፍቅር ፡ ዘርግቶልሃል ።
ከእንቅልፍህም ፡ ይቀሰቅስሃል ፤
ብፁዕ ፡ ነህ ፡ ብትነቃለት ።

ረስቲን ።

Come to the Savior
S.S. 1165

ያ፩ ህ

S.T. 625. Am. 38.

፩ ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ ና ፡
መንገዱን ፡ ያስተምርሃል ።
ከኛ ፡ ጋራ ፡ ይቆማል ፤
ይመሃልም ፡ ና ።
ደስታ ፡ ደስታ ፡ ይሆናል ፤
ኃጢአታችን ፡ ያጠፋል ፡
በሴታችን ፡ በሰማይ ፡
ሁላችን ፡ ስንኖር ።
፪ ፡ ስሙ ፡ አውን ፡ ነገሩን ፤
አኩሩት ፡ በልባችሁ ፤
መቅደሱን ፡ ሊሠራ ፡ ነው ፡
በልባችሁ ።
ደስታ ፡ ደስታ ፡ . . . ።
፫ ፤ ገና ፡ ዛሬ ፡ ከዚህ ፡ ነው ፤
ገና ፡ ቅርብ ፡ በፍቅሩ ።
ስሙ ፡ አውን ፡ ይጠራል ፤

ኑ ፡ ሁላችሁ ።
ደስታ ፡ ደስታ ፡ . . . . ።

ሉንዳል ። B.V.

፻፷፬ ለ

S. T. 625. Am. 88.

፩ ፡ የሱል፡ ሲጠራህ ፡ ወደ ፡ ሰማይ፡
ቸኩል ፡ ወደርሱ ፡ ሳትዘገይ ።
መንገዱንም ፡ ያስተምርሃል ፡
ፍቅሩም ፡ ይታይሃል ።
ምን ፡ ይሆናል ፡ ለሰማይ ፡ መናኝ ፡
ድሮ ፡ ከምላክ ፡ ጋራ ፡ ሲገናኝ ።
ምን ፡ ያህል ፡ ደስታ ፡ አለ ፡ በላይ ፡
በቤቱ ፡ በሰማይ ።
፪ ፡ ዛሬም ፡ በታሉ ፡ ቀርቦልሃል ፡
ዛሬም ፡ እረኛህ ፡ ፈልጎሃል ።
ሰምተሃል ፡ ድምጹን ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡
ልብህን ፡ ከፈትክ ፡ ወይ ፡
ምን ፡ ይሆናል ፡ . . . ።

፫ ፡ ሳታመነታ ፡ ለርሱ ፡ ክፈት ፡
ዛሬም ፡ ተቀበል ፡ ከርሱ ፡ ስርየት ።
ዛሬ ፡ ሲሰጥህ ፡ ያምላክ ፡ ጸጋ ፡
ልብህን ፡ አታዝጋ ።
ምን ፡ ይሆናል ፡ . . . ።

ረስቲን ።

፻፷፭

S. T. 301.

፩ ፡ የሱስ ፡ መድኃኒትህ ፡
ልቡን ፡ ከፍቶልህ ፡
በቅፉ ፡ ሊቀበልህ ፡ ምኞቱ ፡ ነው ።
ምሉ ፡ ደኅንነትም ፡ ከተገኘልህ ፡
ስለምን ፡ ጭንቁን ፡ የምትመርጠው ፡
ታላቅ ፡ መሐሪው ፡ አንተን ፡ ይጠራል ፡
ልብህን ፡ ስጠኝ ፡ በፍቅሩ ፡ ይላል ።
ስለምን ፡ ጸጋው ፡ በከንቱ ፡ ይቀራል ፡
ነፍስንም ፡ ላንተ ፡ ሲል ፡ ለውጥዋል ።

፪ ፤ ጸድቅዋል ፡ ዓለም ፡
በጌታ ፡ በየሱስ ፤
የኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ቀርብዋል ።
ቅዱሱ ፡ ረከሰ ፡ እኛን ፡ ሊቀድስ ፡
መ-ቶም ፡ ሁላችንን ፡ አድኖናል ።
ደመ ፡ ሲፈስ ፡ ተደመሰሰ ፡ ዕዳው ፡
ኃጢአታችንም ፡ ጠፍቶልናል ።
ስለሥረኞች ፡ ፈራጁ ፡ ተቀጣ ።
ታረቀ ፡ አምላክ ፡ ይበቀንማል ።

፫ ፤ አሁን ፡ ለኃዋአን ፡ ብዕዕና ፡ ተሰጠ ፤
የበደላችን ፡ እጥፍ ፡ ሁንዋል ።
አዳም ፡ ሁላችንን ፡ እንዳበላሸ ፡
ክርስቶስ ፡ ሁላችንን ፡ አብጅትዋል ።
ምሉ ፡ አርነት ፡ ያገኙቱ ፡ ባሮች ፡
ወደው ፡ ሊገዙ ፡ ይገባ ፡ ይሆን ፤
እኛስ ፡ ይልቅ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡
እንደ ፡ ልጆች ፡
ቸር ፡ አባታችንን ፡ እናመስግን ።

፬ ፤ ፍቁር ፡ መድኃኒቱ ፡ ሆይ ፡
ትሩፋትህ ፡
ለኔ ፡ ተሰጠና ፡ የኔ ፡ ይሁን ።
ስሜ ፡ ተጽፍዋል ፡ በመጽሐፍህ ፡
ከልቤም ፡ አንሥተሃል ፡ ሽክሙን ።
አባትህን ፡ ሳትክድ ፡ ራስህንም ፡
ስሜን ፡ ከቀ-ስልህ ፡ አትፍቅም ።
ፍቅርህን ፡ ላክብረው ፡
እንዲህ ፡ ልበልም ፤
ወጽመዱን ፡ በጠስክ ፡ አመጣኸኝም ።

ረስቲን ።

ጀነፌ

S. T. 793. 330.

፩ ፤ የየሱስ ፡ ልብ ፡ ተክፈተልህ ፡
በምሕረቱም ፡ ይጠራሃል ።
የምስኪኑ ፡ ወዳጅ ፡ ራራልህ ፡
መድኃኒትም ፡ ይሰጥሃል ።
ቃሉን ፡ አሁን ፡ ስታደምጸው ፡
ልብህን ፡ አታደንዝዘው ።

፱ ፤ አሁን ፡ ይጠራሃል ፡ በፍቅር ፡
አሁን ፡ መድኃኒታችን ፡ ነው ።
አንድ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ መጥቶ ፡ በክብር ፡
ሲጠራህ ፡ ፊራኃችን ፡ ነው ።
ዛሬ ፡ እርሱን ፡ ተቀብለህ ፡
ለፍርድ ፡ ሲጠራህ ፡ ብፁዕ ፡ ነህ ።
ፈጽቷል ።

የአጼ

S. T. 287. Am. 89.

፩ ፤ የልብህን ፡ በር ፡ የሚመታ ፡
ማን ፡ ነው ፤ ማን ፡ ይጠራል ፤
በደሙ ፡ የገዛህ ፤ መድኃኒትህ ፡ ነው ፤
በፍቅሩ ፡ ለአንተም ፡ ይራራል ።
፪ ፤ በፊትም ፡ ሲጠራህ ፡
ሲፈልግህም ፡ ሰምተሃል ፡ ወይ ፤
ለጌታህ ፡ ለርኅሩኅ ፡ መድኃኒትህም ፡
የልብህን ፡ በር ፡ ከፍተሃል ፡ ወይ ፤
፫ ፤ የዓለም ፡ ከንቱነት ፡
የልብህን ፡ ራብ ፡ አያርቅም ።

ወዳለምም ፡ ደስታ ፡ ፈቃድህ ፡ ሲሰብ ፡
መባበት ፡ ከልብህ ፡ አይለቅም ።
፬ ፤ የዓለምን ፡ ሁሉ ፡
ብዕልና ፡ ከብት ፡ ብትወርስም ፡
በምድሩ ፡ ብቻ ፡ ካገኘኸው ፡ ሀብት ፡
ሰላም ፡ ወደ ፡ ልብህ ፡ አይደርስም ።
፭ ፤ በሰው ፡ ወዳጅነት ፡
በዓለምም ፡ ሽር ፡ ብትመራ ፡
ረድኤት ፡ ስትሻ ፡ ሳታገኝ ፡ ብትቀር ፡
ያጋልጡሃል ፡ ስትጠራ ።
፮ ፤ ግን ፡ የሱስ ፡ ቢሰጥህ ፡
የእውነት ፡ ሰላም ፡ ለዘላለም ፡
ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሀብት ፡ አትሻም ፤
አይተውህምም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ።
፯ ፤ የየሱስ ፡ ወዳጅ ፡
ከመሆን ፡ የሚበልጥ ፡ ምን ፡ ይገኛል ፤
የፍቅሩን ፡ የጸጋውንም ፡
መብለጥ ፡ ሲገልጥ ፡

ክእርሱ ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ያስመኛል ፤
ፀ ፡ ብፅዕናን ፡ ሊሰጥህ ፡
ለመጣው ፡ ወዳጅ ፡ ክፈትለት ።
ለአንተም ፡ ብፅዕናህን ፡ ሰያዘጋጅ ፡
የሰጠህን ፡ ተቀበልለት ።

ረስቲን ።

Whosoever will live. 206

፪፻፳

S. T. 299.

፩ ፤ የሚሰማ ፡ ሁሉ ፡
ድንቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡
ይድረስ ፡ በምድርም ፡ ለሁሉ ፡ ሰው ።
እያንዳንዱ ፡ ይምጣ ፡ ወደ ፡ ይቅርታው ፤
የራቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ ኑ ።
ብትወዱ ፡ ኑ ፡ ብትወዱ ፡ ኑ ፤
ይሰማል ፡ በስፍራው ፡ ሁሉ ፡
ለሚወድ ፡ ለጠፋ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡
ተመለስ ፡ ይለዋል ።
የራቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ ኑ ።

፪ ፤ ለሚወድም ፡ ሁሉ ፡
ይህ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።
ከእኔ ፡ ጸጋዬን ፡ በከንቱ ፡ ያገኛል ።
እርሱም ፡ ይሄዳል ፡
ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፤
የራቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ ኑ ፡ . . . . ።
ብትወዱ ፡ ኑ ፡ . . . ።
፫ ፤ የሚመጡ ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ ቸኩሉ ፤
ደጁ ፡ አሁን ፡ ክፍት ፡ ነው ፡
ደግሞ ፡ መንገዱ ።
በየሱስ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ አትለፉ ፡
የራቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ ኑ ፡
ብትወዱ ፡ ኑ ፡ . . . . ።

ሶንዳል ።

፪፻፳፱

S. T. 287. Am. 89.

፩ ፤ በተስፋ ፡ ስቀርበው ፡
ለመስማት ፡ ቃሉን ፡
ያብራልኝ ።

የጨለማ ፡ ኃይልም ፡ ይርቃል ፡ ከኔ ፡
የብርሃኑም ፡ ሕይወት ፡ ይገኛል ።
፪ ፡ በፍቅርና ፡ መንፈስ ፡
ይጠራል ፡ ዛሬ ፡
ሳይቈጣ ።
ለማሰማትም ፡ ክፈት ፡ ልብህን ፡ አሁን ፡
በንቃትም ፡ አድምጠው ፡ ቃሉን ።
፫ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡
ይሰጣል ፡ ዛሬ ፡
ለልጆቹ ።
አሁን ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ይሰጣል ፡ ጽድቁን ፡
ድኖችም ፡ ደግሞ ፡ ያገኛሉ ።
፬ ፡ ከኃጢአት ፡ ባርነት ፡
ለማውጣት ፡ ቶሎ ፡
ደክሞችን ።
ከብዶኑ ፡ ሲኖር ፡ የኃጢአት ፡ ቀንበር ፡
በጸጋው ፡ ይፈታናል ፡ አሁን ።

ተወልደ ፡ ብርሃን ።

Acts. 410 Work for the Night S.S. 778

S. T. 548. Am. 58.

፩ ፡ ኑ ፡ ደክሞች ፡ ሁላችሁ ፡
ወዴ ፡ ምሉ ፡ ሰላም ።
ሕይወት ፡ የሚሰጣችሁ ፡
ወረታ ፡ አይሻም ።
ግሩም ፡ ነው ፡ የምሕረቱኛ ፡
የፍቅሩ ፡ ትሩፋት ፡
የሚሰጠን ፡ ለኛ ፡
በጸጋው ፡ ብዛት ።
፪ ፡ የሱስን ፡ እየው ፡ ቶሎ ፡
አሁን ፡ ይጠራሃል ።
ብትዘገይስ ፡ ቶሎ ፡
ዘመንህ ፡ ያልፋል ።
ፍቅሩን ፡ አትናቀው ፡
አሁን ፡ ተቀበለው ፡
ገዝቶሃልና ፡ ለርሱ ፡
ልብህን ፡ ስጠው ።

ሮ ፣ ቸኩል ፣ ወደርሱ ፣ አሁን ፤
አንተን ፣ ይጠብቃል ።
የተዘጋጀ ፣ ክብሩን ፣
ያቀርብልሃል ።
ባዶ ፣ ምስኪን ፣ መሆንህን ፣
እርሱ ፣ ቤጣም ፣ ያውቃል ።
የሚያስፈልግህን ፣
ወዶ ፣ ይሰጣል ።

ተወልደ ፣ ብርሃን ።

፻፴፩

S. T. 36. Am. 90.

፩ ፣ ያባትህ ፣ ዕቅፍ ፣ ተከፍትዋል ፣
ልጁን ፣ ሊቀበልህ ፤
በስምህም ፣ ይጠራሃል ፣
በፍቅሩም ፣ ፈለገህ ።
እጁንም ፣ ዘርግቶልሃል ፣
በታላቅ ፣ ምሕረት ።
ለአንተም ፣ ተዘጋጅትዋል ፣
ስፍራ ፣ በሠርጉ ፣ ቤት ።

፪ ፣ በዚህ ፣ በዓለም ፣ በረሃ ፣
ሰላም ፣ የማታገኝ ፣
ከሕይወት ፣ ምንጭ ፣ ጥሩ ፣ ውኃ ፣
እንደሌት ፣ የማትመኝ ፣
በሌላ ፣ ምንጭ ፣ የልብህ ፣ ጥም ፣
ሊጠፋ ፣ አይችልም ።
መድኃኒት ፣ ያለ ፣ የሱስ ፣ ስም ፣
አልተገኘልንም ።
፫ ፣ ርስትህን ፣ ሁሉ ፣ በትነህ ፣
መሞት ፣ ያስፈራሃል ።
በቤትህ ፣ ግን ፣ ቸር ፣ አባትህ ፣
ልጁን ፣ ይጠብቃል ።
የሠርግ ፣ ልብስና ፣ ቀለበት ፣
አሁን ፣ ይቆይሃል ።
በከንቱ ፣ ሁሉን ፣ ለመስጠት ፣
አባትህ ፣ ወድዋል ።
፬ ፣ የጠፋ ፣ ልጅ ፣ ወዳበቱ ፣
ቢሔድ ፣ በንስሓ ፣

በማይመረመር ፡ ምሕረቱ ፡
ይወርሳል ፡ ፍሥሓ ።
በቤቱም ፡ ሁሉ ፡ ግሩም ፡ በዓል ፡
እልልታም ፡ መዝሙርም ፡
በዚያ ፡ ቀን ፡ ይደረጋል ፤
ደስታውም ፡ አይተረክም ።

ረበቱን ።

፻፸፪

S. T.765.

፩፡በመላ፡ዓለም፡ጭንቀት፡ይበዛል፤
በሽታና ፡ ድካም ፡ መልቶበታል ።
ጦር ፡ መረረን ፡ ኃጢአት ፡ ይገሩል ፤
ፈተና ፡ ቀርቦ ፡ ይሸምቃል ።
፪፡በዬት፡ይገኛል፡ሕይወት፡ለሞቱ፤
መድኅን ፡ ለሕሙም ፡ ኃይል ፡ ለዛሉ ፤
ምግብ ፡ ለተራቡ ፤ ደስታ ፡ ለባቡ ፤
ድፍረት ፡ ለፈሩ ፡ ለደከሙ ፡ ፤
፫፡ ወንጌልን፡ስሙ፡የሱስ፡ሲጠራ፤
ሁሉ ፡ ወደኔ ፡ አሁን ፡ ይምጣ ።

ራብተኛ ፡ ይጥገብ ፡ ጥማተኛ ፡ ይርካ ፤
ኅዙን ፡ ይቀበል ፡ ቅዱስ ፡ ደስታ ።
፬፡ እርሱ ፡ ሞተልን ፡ አስታረቀን ፤
አፍስሶ ፡ ደሙን ፡ ሊዋጀን ።
ጽድቅን ፡ አመጣ ፡ ሰላም ፡ አስገኘ ።
ጸጋን ፡ ይሰጣል ፡ ለታመነ ።
፭፡ ጤናና ፡ሕይወት ፡የሚፈስበት ፡
ያደርገናል ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡
ያሳድረናል ፡ ፍቅር ፡ ቸርነት ።
የሱስ ፡ አግባልን ፡ ጽኑ ፡ እምነት ።

O. E.

፻፸፫

Am. 119.

፩ ፡ እንደ ፡ ቅርምጥ ፡ ብትሆን ፡
የልባችሁ ፡ ኃጢአት ፡
እንደ ፡ ደም ፡ ብትቀላ ፡
እንደ ፡ ጥጥ ፡ ትነጣለች ፡
እንደ ፡ ነጭ ፡ ጥጥ ፡ ትሆናለች ፡

እንደ ፡ በረዶም ።
እንደ ፡ ቅርምዝም ፡ ብትሆን ፡
እንደ ፡ ደም ፡ ብትቀላ ፤
ትነጣለች ፡ እንደ ፡ ጥጥ ፡
እንደ ፡ በረዶም ፡ ደማሞ ።
፪ ፤ አትርሳኝ ፡ ፈጣሪህ ፡ ነኝ ፡
አሁንም ፡ እንተያይ ።
እንደ ፡ ደመና ፡ ይጠፋል ፡
ያለህን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ።
እኔ ፡ ነኝ ፡ ሌላም ፡ የለህም ፡
የሚያድንህ ።
እሺ ፡ ብለህ ፡ ብትታዘዝ ፡
በረከትን ፡ ታገኛለህ ፡
በፍርድም ፡ ትድናለህ ፡
ፈጽሞም ፡ ትነጻለህ ።
፫ ፤ አትፍራ ፡ ትድናለህ ፤
በስምህ ፡ ተጠርተሃል ።
እጅጌም ፡ ዘርግቻለሁ ፡

ምርኩዝ ፡ ይሆንልህ ፡ ዘንድ ።
ኃጢአትህን ፡ ያጠፋሁልህ ፡
እኔ ፡ ብቻ ፡ ነኝ ።
አትፍራ ፡ ገዝቼሃለሁ ፡
በስምህ ፡ ጠርቼሃለሁ ፡
የኔ ፡ ነህ ፡ ልዘላለም ፡
ለዘላለም ፡ የኔ ፡ ነህ ።

Majestic Sweetness
Ans. 369 ፻፴፩

S. T. 308. Am. 64.

፩ ፡ ቀጭን፡ሆነች፡የሕይወት፡ደጅ፡
ያች ፡ መንገድ ፡ ጠባብ ፡ ናት ።
ተጋደል ፤ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፤
በዚያ፡ለመግባት፡በዚያ፡ለመግባት።
፪ ፤ ሰማይም ፡ ገና ፡ አልመላም ።
ስፍሮች ፡ ገና ፡ አሉ ።
ሊከፈቱ ፡ በየሱስ ፡ ስም ፡
ደጆቹ ፡ ለሁሉ ፡ ደጆቹ ፡ ለሁሉ ።
፫ ፤ ነጭ፡ልብስ፡ለብሰው፡በሰማያት፡
ብዙ ፡ አእላፋት ፡

ይቆማሉ ፡ በዙፋን ፡ ፊት ።
ላንተም ፡ አለህ ፡ መግባት ፡
ላንተም ፡ አለህ ፡ መግባት ።
፬ ፡ በየሱስ ፡ ልብ ፡ በገነቱ ፡
አለ ፡ ገና ፡ ስፍራ ።
ይጠራኛል ፡ በወንጌሉ ፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ደስታ ፤
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ደስታ ።
፭ ፡ በዚያም ፡ አገር ፡ በጸጥታ ፡
ተመችቶኝ ፡ ልኖር ።
ብፁዕ ፡ እርሱ ፡ የሚሰማ ፡
የአምላክን ፡ ምክር ፤
የአምላክን ፡ ምክር ።

ሉንዳል ።

The Home Over There
S. S. 942
Br. 43

የ፴፩ኛ

Am. 129. S. T. 677.

መክ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ፫ ።

፩ ፡ ሰባኪው ፡ አለ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ የሚሠራው ፡

ደስ ፡ የሚለውና ፡ የሚያገኘው ፡
ሁሉም ፡ በቶሎ ፡ ሊያልፍ ፡ ነው ።
ከንቱ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡
ሰባኪው ፡ አለ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡
ከንቱ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀብት ፡
ከንቱ ፡ ነው ።
፪ ፡ እንደ ፡ ነዋሪ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡
ስደክም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ንብረት ፡
ና ፡ ብለህ ፡ ብትጠራኝ ፡ በቅዕበት ፡
ምን ፡ ልመልስ ፡ ነኝ ፡ በአንተ ፡ ፊት ፡
ከንቱ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ . . ።
፫ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ሆይ ፡ ለምንህ ፡
መዝገብን ፡ ትሰበስባለህ ፡
ዛሬ ፡ ግታ ፡ ትፈልጋለህ ፡
ልትሔድ ፡ በሞት ፡ ኃይል ፡ ተይዘህ ።
ከንቱ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ . . ።
፬ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከንቱን ፡ ይመስላል ፡

ዘመኑም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ያልፋል ፡
በቅዕበት ፡ አበባው ፡ ይረግፋል ፡
መታሰቢያውም ፡ ይጠፋል ።
ከንቱ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ . . ።
ቁ ፡ ፩ ፡ ያ ።

ንስሐና ፡ መመለስ ።

ያዕቆ

S. T. 281. Am. 131.

፩ ፡ አ ፡ አምላኬ ፡
በኃጢአቱ ፡
መንፈሴ ፡ አዘነብኝ ።
በዚች ፡ ዓለም ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ የለም ፡
በጭንቀት ፡ የሚረዳኝ ።
፪ ፡ ሩቅም ፡ ብሔድ ፡
ረጅም ፡ መንገድ ፡
እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡
በየት ፡ ላግኝ ፡

ደስ ፡ የሚለኝ ፡
ከኃዘን ፡ የሚፈታ ።
፫ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ቸር ፡ አምላኬ ፡
እቀርባለሁ ፡ አሁን ።
አባት ፡ ሁነኝ ፡
ተዓገሠኝ ።
ዘወትር ፡ ሁንልኝ ፡ ተገን ።
፬ ፡ ቸሩ ፡ የሱስ ፡
ልሆን ፡ ዕጉሥ ፡
ለውጥ ፡ ክፉ ፡ ጠባዬን ።
ደካማ ፡ ነኝ ፡
አራምደኝ ፡
በደስታ ፡ ወይ ፡ በኃዘን ።
፭ ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡
በቅን ፡ መንገድ ፡
ልሔድ ፡ እጄን ፡ ያዝልኝ ።
በዚች ፡ ዓለም ፡

ብርቱ ፡ ሽክም ፡
ልታገሥ ፡ ኃይልን ፡ ስጠኝ ።
፮ ፡ አብና ፡ ወልድ ፡
በባሕርይ ፡ አንድ ፡
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡
ስማኝ ፡ አሁን ፡
አዎን ፡ አሜን ፡
ጸሎቴን ፡ ትሰማለህ ።

ሉንዳል ።

ያዕቆብ

S. T. 280.

፩ ፡ ከከበደ ፡ ኃጢአቴ ፡
ወደኋት ፡ ልሸሽ ፤ አ ፡ አምላኬ ፤
በጣም ፡ እጨነቃለሁ ።
ሕግህን ፡ ሁሉ ፡ አፍርሼ ፡
ሩቅም ፡ ከአንተ ፡ ሸሽቼ ፡
ፍርድህን ፡ እፈራለሁ ።
ነፍሴንም ፡ ኃዘን ፡ ደቄሰው ፡

ልቤንም ፡ ጸጸት ፡ ሰበረው ።
አ ፡ ጌታዬ ፡ ራራልኝ ፡
መድኃኒትም ፡ ሁንልኝ ።
፪ ፡ አ ፡ የሱስ ፡ ቃልህ ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤
ለነፍሴ ፡ ጤናም ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፤
ልቀበለውም ፡ እሻለሁ ።
ወዳለም ፡ የሱስ ፡ መጥትዋል ፤
ዕዳዬን ፡ ከፈለ ፡ ይላል ፤
በእርሱም ፡ እድናለሁ ።
ቀማኛውን ፡ የተቀበለው ፡
በገነትም ፡ ያሳረፈው ፡
እኔንም ፡ እንዲቀበል ፡
ይለኛል ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ።
፫ ፤ አ ፡ የሱስ ፤ አ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፤
ወደ ፡ አንተ ፡ ዓይንና ፡ እጅ ፡
እኔ ፡ እዘረጋለሁ ።
የረከስሁ ፡ እኔን ፡ አጥራኝ ፤
ከኃጢአትም ፡ እድፍ ፡ አንጻኝ ።

በአንተ ፡ አምናለሁ ፤
የጠፋ ፡ በግም ፡ ነበርሁኝ ፤
በአንተ ፡ ግን ፡ ተገኘሁኝ ።
አኑረኝ ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡
አንተ ፡ የምትራራ ።

ክፍል ፡ አግዚኦ ።

፻፸፭

S. T. 275.

፩ ፡ አ ፡ ርኅሩኅ ፡ አምላክ ፡
ጸጋህን ፡ ስጠኝ ፡
ኵነጠአትም ፡ በርሱ ፡ አድነኝ ።
፪ ፡ የሱስ ፡ መንፈስህንም ፡ ላክልኝ ፡
በፈተህም ፡ ምሕረትህ ፡ ይቁምልኝ።
፫ ፡ ያለም ፡ ብርሃን ፡
እንደ ፡ ጥዋቱ ፡ ኮከብ ፡
የምድር ልጆችን መዳንን ለማቅረብ፡
ከወጣህ ፡ አንተን ፡ እመለከታለሁ ፤
በደስታም ፡ ፈራህን ፡ እከተላለሁ ።

፬ ፡ በኵነጠአት ፡ እንቅልፍ ፡
ለማንቀላፋት ፡
ሞትም ፡ ልሞት ፡ አልተውኸኝም ፡
አ ፡ አባት ።
በጸጋህ ፡ ስለሰጠህ ፡ ምሕረትን ፡
ተቀበል ፡ ልቤን ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ።
፭ ፡ መድኃኒት ፡ ሆይ ፡
ለእኔና ፡ ለሁሉ ፡
የመቅሠፍት ፡ ጽዋን ፡
ጠጣኸው ፡ በምሉ ።
እወደሃለሁ ፡ በንተም ፡ አምናለሁ ፡
በኃይልህም ፡ከውድቀት ፡እድናለሁ።

ረዳቴን ።

፻፸፮

S. T. 12. Am. 66.

፩ ፡ ና ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡
ልቤን ፡ አሙቀው ።
የክብር ፡ ንጉሥ ፡ ጣዖትን ፡ አርቀው።

በውስጤም ፡ ንገሥ ፡
ኃጢአቴን ፡ ፋቀው ። ።
ና ፤ ጌታ ፡ የሱስ ። ።
፪ ፤ አ ፡ ቸር ፡ ወዳጄ ፤
መንፈሴን ፡ ጐብኘው ። ።
አንተ ፡ ነህ ፡ ረጅ ፡ ደስ ፡ የምታሰኘው ።
ጸጋህን ፡ ከእጅህ ፡ አሁን ፡ እንዳገኘው ፤
ና ፤ ጌታ ፡ የሱስ ። ።
፫ ፤ ና ፤ ደስ ፡ አሰኘኝ ፡ በኃዘን ፡ ሁሉ ።
ፍርሃት ፡ ሲይዘኝ ፡ ጭንቀትም ፡ ምሉ ፡
ና ፡ ጌታ ፡ አድነኝ ፡ ከሚጐዳኝ ፡ ሁሉ ።
ና ፤ ጌታ ፡ የሱስ ። ።
፬ ፤ የሱስ ፡ ሲመጣ ፡
በማይወሰን ፡ ክብር ፡
ልቡ ፡ የነጻ ፡ ሊያገኝ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፤
በቶሎ ፡ ይምጣ ፤ ይቅረብ ፡ በፍቅር ። ።
ና ፤ ጌታ ፡ የሱስ ። ።

ሉንዳል ።

፪ኛ

S. T. 12. Am. 66.

፩ ፤ ሕግ ፡ ፈረደብን ፤
ምሕረት ፡ እንለምን ።
ጸጋህን ፡ ለግስ ፤
ፍርድን ፡ ስንለብስ ። ።
ትል ፡ ነን ፡ እኛ ፤
የሚበን ፡ ትቢያ ፡
አላፊ ፡ ጥላ ። ።
፪ ፤ ጠግግ ፡ ከብዶን ፤
ኃጢአት ፡ ወረሰን ፤
ምኞትም ፡ ነዳን ፤
ፈተና ፡ አሳተን ። ።
ደክሞች ፡ ነን ፤
አትቅሠፈን ። ።
ተቀበለን ። ።
፫ ፤ ስለ ፡ ሥቃዩ ፤
ስለ ፡ እሾህ ፡ ዘውዱ ፡
የሱስ ፡ የጫነ ፤

ሊያስታርቀኝ ፥
አምላክ ፥ ራራልን ፤
አትፍረድብን ፥
አባት ፥ ሁንልን ።
፬ ፥ በቅዱስ ፥ ደሙ ፥
የወጣ ፥ ከጐኑ ፥
እንድናለን ፥
ይጠጋል ፥ ቍስላችን ።
የዋህ ፥ እረኛ ፥
የከዳውን ፥ ጠራ ፥
ና ፥ ወደ ፥ መንጋ ።
፫ ፥ አምላክ ፤ እርዳኝ ፥
በየሱስ ፥ ማረኝ ።
ሲማልድልን ፥
ጸሎቱን ፥ ስማልን ።
እንጮኻለን ፥
ደምስስ ፥ ኃጢአታችንን ፥
አምላክ ፥ እይልን ።

O.E.

What a Friend
S. S. 319
Unc. 384

ያጣፅ

S. T. 35. Am. 154.

ኃጢአቴ ፥ ያሳዝነኛል ፥
ነፍሴንም ፥ ያከብዳል ።
እንደ ፥ ሕማም ፥ ይቀፈኛል ፥
ኃይሴን ፥ ያደነዝዛል ።
ዓመፃዬን ፥ ደምስስልኝ ፤
እንዳልኰንን ፥ አድነኝ ።
ፍጠርልኝ ፥ ቅዱስ ፥ አሳብ ፥
ልቤን ፥ ወደ ፥ አንተ ፥ ሳብ ።

O.E.

ያጣፀ

S. T. 475.

፩ ፤ ተነሥቼ ፥ ወዳባቴ ፥ ልሔድ ፥ ነኝ ፤
በቀና ፥ መንፈስ ፥ ላድርግ ፥ ኑዛዜን ።
አምላኬ ፥ ሆይ ፤ ምሕረትህን ፥ አሳየኝ ፤
በጸጋ ፥ ደምስስልኝ ፥ ኃጢአቴን ።
፪ ፤ እንዲህ ፥ ብዬ ፤ አባቴ ፥ ሆይ ፤
ተውልኝ ፥

ባንተና ፡ በሰማይም ፡ በደልሁ ።
ሰላም ፡ ስጠኝ ፤
ደስታህን ፡ አውርድልኝ ፤
ተቀበለኝ ፤ ስል ፡ እጮኻለሁ ።
፫ ፡ ይሰማኛል ፡ ኃጢአቱ ፡ እንደ ፡ በዛ ፤
የአምላክ ፡ ምሕረት ፡ ገና ፡ ይበልጣል ።
ጥፉ ፡ ልጁ ፤ ልመለስ ፡ ሲል ፡ ቢነሣ ፤
ቸር ፡ አባቱ ፡ ዓቅፎ ፡ ይቀበላል ።
፬ ፡ ተነሥቼ ፡ ወዳባቴ ፡ ልመለስ ፤
ልግጠን ፡ ነኝ ፡ በአባትነቱ ።
ጉባኤ ፡ ብፁዓን ፡ ላምላክ ፡ ሊወድስ ፤
ሲገባ ፡ ጥፉ ፡ ልጅ ፡ በማኅበሩ ።

O.E.

From Greenland's icy Mts.
S.S. 1070 b

የማር ፡ S. T. 349.

፩ ፤ የሱስ ፡ ኃጢአቱን ፡ ወስዶ ፡
በመስቀል ፡ እስከ ፡ ሞት ፤
ለኔ ፡ አርነት ፡ ሰጠ ፡

ከፍርድ ፡ ከሞኔ ፤
ለየሱስ ፡ ዕዳዬን ፡
አሁን ፡ አስታውቃለሁ ።
በክቡር ፡ ደሙ ፡ ብቻ ፡
ኃጢአቱን ፡ ያጠፋል ።
፪ ፤ ክብደቱ ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡
አሁን ፡ እሸከማለሁ ።
ከእርሱ ፡ ረድኤት ፡ አለኝ ፡
በታላቅ ፡ ምሕረቱ ።
ድካም ፡ ከችግር ፡ ሁሉ ፡
ለየሱሴ ፡ ብሰጠው ፤
እርሱ ፡ ከትልቅ ፡ ጎዘን ፡
ሊረዳኝ ፡ የሚችል ።
፫ ፡ ተስፋዬን ፡ በየሱስ ፡
አድርጌያለሁ ።
በቀኝ ፡ እጁ ፡ ሲይዘኝ ፡
አንዳችን ፡ አልፈራም ።
ያ ፡ ድንቅ ፡ ስም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፤

ልዑል ፡ አማኑኤል ፡
ለነፍሴ ፡ መጸናናት ፡
ሲሆን ፡ ይበቃኛል ።
፬ ፡ የሱስንም ፡ ልመስል ፡
በትሕትና ፡ ግርነት ፡
እንደ ፡ የሱስ ፡ ልሆንም ፡
ብሁሉ ፡ ኑሮዬ ፡
ዘመኔ ፡ ሲጨረስ ፡
ወደ ፡ አእላፋት ፡
ምእመናን ፡ ልደርስ ፡
ልኖር ፡ በደኅንነት ።

ሉንዳል »

I am Coming to the Cross S.S. 477 Une. 361

የማ፬ ፡ Am. 14.
፩ ፡ መጣሁ ፡ ወደ ፡ መስቀልህ ፡
ምስኪን ፡ ነኝ ፡ ደክማም ፡ ነኝ ፡
ወዳንተ ፡ እንድቀርብህ ፡
አ፡መድኃኒቴ ፡ እርዳኝ ።
ባንተ ፡ አምናለሁ ፡

ቡሩክ ፡ የቀራንዮ ፡ በግ ።
ተንበርክኬ ፡ በጸሎት ፡
አድነኝ ፡ የሱስ ፡ አድነኝ ።
፪ ፡ ያለኝንም ፡ ሰጠሁህ ፡
የምድር ፡ መዝገቤንም ፡
ሥጋና ፡ ነፍስ ፡ ላንት ፡ ሊሆን ፡
ለዘላልም ፡ ሁሉን ፡ ላንት ።
ባንተ ፡ አምናለሁ ፡ .
፫ ፡ በተስፋህም ፡ አምናለሁ ፡
እርዳኝ ፡ ስለሞትህልኝ ።
በምድር ፡ ሟንቀት ፡ አለሁ ፡
አ ፡ የሱስ ፡ እጄን ፡ ያዘኝ ።
ባንተ ፡ አምናለሁ ፡ .
፬ ፡ የሱስ ፡ ነፍሴን ፡ ያድናታል ፡
በርሱ ፡ የጸናሁ ፡ ነኝ ።
እሄ ፡ በርሱ ፡ ድኛለሁ ።
ለበጉ ፡ ክብር ፡ ይሁን ።
ባንተ ፡ አምናለሁ ፡ .

ባ፡ን ።

ያሜን

S. T. 4. Am.113.

፩ ፤ አ ፡ የሱስ ፤ የሕይወት ፡ ውኃ ፡
የጸጋ ፡ ምንጭ ፡ ሆንህልኝ ።
ልቤ ፡ የለመነውን ፡ ስማ ፡
በጸጋም ፡ ፈጽምልኝ ።
ታላቅ ፡ ፍቅርህ ፡ ግሩም ፡ ስምህም ፡
የከፈትህልኝ ፡ ዕቅፍህም ፡
ለነፍሴ ፡ ድፍረት ፡ ሰጠ ።

፪ ፤ አ ፡ የሱስ ፤ ወደ ፡ መስቀልህ ፡
እጄን ፡ እዘረጋለሁ ።
ዓይኔንም ፡ ወደ ምህረትህ ፡
በተስፋ ፡ አነሣለሁ ።
የዕውቀት ፡ ዛፍ ፡ ያፈራውን ፡ ፍሬ ፡
በመስቀል ፡ ዛፍ ፡ አ ፡ መድኅኔ ፡
ከለቀምኸው ፡ ጠፋልኝ ።

፫ ፤ ተመስገን ፤ ቸር ፡ መድኃኒቴ ፡
ፍርደኔን ፡ ተሸከምህልኝ ።

በማይመረመር ፡ ርኅራኄ ፡
ሞቴን ፡ ተቀብልህልኝ ።
ያጠፋሁትን ፡ ከፈልኸው ፤
ሰማይን ፡ ለኔ ፡ ከፈትኸው ፡
ስምህን ፡ እንዳከብር ።

፬ ፤ ዓይኔም ፡ ሲዘጋ ፡ አካሌም ፡
ወደ ፡ መሬት ፡ ሲመለስ ፡
ከመከራ ፡ ከትካዜም ፡
ድኜ ፡ አንተን ፡ ልወድስ ።
ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስም ፡
ይሁን ፡ ምስጋና ፡ ውዳሴም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ። አሜን ።

ረዕቲን ።

ያሜን

Savior like a Shepherd S.S. 1164
Am. 99. Eth. 38

፩ ፤ ቸሩ ፡ ጠባቂ ፡ ምሪኔ ፡
በጥሩ ፡ ቃልህ ፡ ብርሃን ፤
ከመከራ ፡ ጠብቀኝ ፤

በምሕረትህ ፡ መግበን ።
ቸሩ ፡ የሱስ ፤ ቸሩ ፡ የሱስ ፤
ዕለት ፡ ጠብቅ ፡ መንጋህን ።
፪ ፤ ዕለት ፡ ጠብቀን ፡ መንጋህን ፡
እኛ ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነን ።
ብንስትም ፡ መልሰን ፡
ወደ ፡ ቤትህ ፡ አድርሰን ።
ቸሩ ፡ የሱስ ፤ ቸሩ ፡ የሱስ ፤
ስማ ፡ ጸሎታችንን ።
፫ ፤ አሁን ፡ አትቅሠፈን ፡
በበደላችን ፡ መጠን ፡
ዳሩ ፡ ጸጋህን ፡ ስጠን ፡
ቅዱስ ፡ ደምህ ፡ ይጠበን ።
ቸሩ ፡ የሱስ ፤ ቸሩ ፡ የሱስ ፤
ወደ ፡ አንተ ፡ አቅርበን ።
፬ ፤ ወዳንተ ፡ እንመጣለን ፤
ረድኤት ፡ ሁሉ ፡ ካንተ ፡ ነው ።
ጽኑን ፡ እምነት ፡ ፍጠርልን ፡

ፍቅርህን ፡ ለሁሉ ፡ ሰው ።
ቸሩ ፡ የሱስ ፤ ቸሩ ፡ የሱስ ፤
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ውሰደን ።
ኦንዳል ።

ያማኒ ።

S. T. 290.

፩ ፤ የሰይጣንን ፡ መኖርያ ፡
ክናስብም ፡ ያስፈራል ።
የኑኑናን ፡ መሣቂያ ፡
ልባችንን ፡ ያፈርሳል ።
ወደ ፡ ሲያል ፡ እንዳንጠልቅ ፤
እንቅልፍ ፡ እንዳያጠቃን ፡
የጸጋ ፡ ዘመንህ ፡ ሳያልቅ ፡
እ ፡ አምላክ ፡ አነቃቃን ።
፪ ፤ ዛፍ ፡ ከተጣለ ፡ ከመሬት ፡
ተመልሶ ፡ አይነሣም ።
እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ሰይጣን ፡ ቤት ፡
የጠለቀ ፡ አይወጣም ።